Bro 3322/4 fol

# "ልዩነቶቻችን"

ከብርሃኔ ደመቀ
ሐምሌ 1966 ዓ.ም.

በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበርና በኢዜና/አልጀሪያ/ ፌዴሬሽን የከሰረ የጠቋሚዎች ቡድን ስላሉት ልዩነቶች /ከመነሻው እስከ ሐምሌ 1966 ዓ.ም. ድረስ/ ለአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተጻፈ:

የአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች
መጽሄት ቦርድ
ፖ.ሣ. ቁጥር 3198
10364 ስቶክሆልም
ስዊድን

ዛሬ በኢትዮጵያ የተከፈተው ታላቅ የትግል ምዕራፍ በኛ በተራማጆች ላይ አጅግ ከፍ ያሉ ታሪካዊ አደራ ጥሎብናል:: ይህንን አደራችንን ተቀብለን ጊዜ የሚጠይቀውን ተግባር በሚገባ ለመፈጸም በንቅናቄያችን ውስጥ ከመቼውም ይበልጥ መደማመጥና በቁም ነገሮች ላይ መከራከር ተገቢ ነው:: ነገር ግን አንዳንድ ቡድኖችና ግለሰቦች መደብ ከገመደ ይጉትታሉና አርጋታ ሲጠየቁ ድንፋታ፤ የተጣራ ፖለቲካ ሲፈለግ ውዥንብር የሚማርከው የንዑስ ከበርቴ ዝንባሌያቸው አሸንፏቸው ይታያሉ::

በብዙ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን መከራና ንፁህ ደም እዚህ የደረሰው ስመጥሩው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በነዚህ ንዑስ ከበርቴያዊ ውዥንብር አንድነቱ እንዳይሳሳና ከጊዜው ተግባሩ እንዳይወሰውል ነቅቶ መጠበቅ እያንዳንዱ አባል ላይ የሚወድቅ ታሪካዊ ኃላፊነት ነው:: ይህም የማጋለጥ ተግባር የሁላችንንም ትብብር ይጠይቃል:: ስለዚህም እኛም በመሰለን ባንዳንድ ጊዜያዊ ነጥቦች ላይ ተወስነን ይህን ጽሑፍ እናቀርባለን::

"የኢዛና" እና "የፌዴሬሽኑ" ንዑስ ከበርቴ ደንፊዎች በማህበራችን ላይ የማይሰነዝሩት የክስ ዓይነት፤ የማይቆጥሩት ውሸት፤ የማይጠቀሙበት ፀረ ሬቮሉሽናዊ የትግል ዘዴ እንደሌለ በቅርቡ በወጡት " Some thoughts on the current Situation in Ethihpia" በሚል አርእስት የ"ኢዛና" መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ "በፌዴሬሽኑ" ቡለቲን ቁጥር 5 እና 6 ላይ ያሉት ጽሑፎች በቂ ማስረጃ ናቸው:: ይህ ጽሑፋችን በተለይ የሚወስነው በነዚህ ጽሑፎች ላይ ነው::

የማህበራችን የቆየ ጥረት እነዚህ ደንፊዎች የሚያቀርቡትን የስድብ ጋጋታ እየናቁ በነሱ ውስጥ ተድበስብሰው የሚገኙትን የፖለቲካ አቋሞች እየፈለጉ በነሱ ላይ ብቻ ውይይት ለማድረግ መሞከር ነው:: አሁንም ከዚህ ዓብዩታዊ አቋም አንወጣም:: የቆምንለት የፖለቲካ ትግል ነው:: በዚህ ትግል እንኳን "ከተራማጆች የሚመጣው የስድብ ጋጋታ ይቅርና የአድሃሪዎችም ፋሽስታዊ አመጽ አሳወናበደንም:: ንቅናቄያችን የሚጠነክረው እነሱ በሰደቡን ልክ በመሳደብ አይደለም:: በኛ አስተያየት ንቅናቄያችን የሚጠነክረው በስድብ ጋጋታ ሊሸፋፍኑ የሚሞክሩትን የፖለቲካ አቋም እያጋለጡ ማሳየት ስንችል ነው:: ስለዚህ ነገድ ወደ ፖለቲካ ክርክር ይዘናቸው እንገባለን:: በግልጽ ደብዳቤ መልክ የምናቀርብላቸው ይህ ጽሑፋችን እስከዚህም ለስድባቸው ለመመለስ ወይንም ማህበራችንን ከነሱ መሠረተቢስ ክሶች "ነፃ ለማውጣት" አይደለም:: ዓላማችን ከጽሑፎቻቸው በምናነሳቸው አንዳንድ ነጥቦች ላይ በአውሮፓ ውስጥ የሚደረገውን ክርክር ፈጽሞ ከማያውቁት በ"አሜሪካ" ከሚገኙት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር በቁም ነገር የሚካሄድ ውይይት ለመክፈት ነው:: ስለዚህም በማህበራችን ላይ ለሚሰነዝሩት መሰረተቢስ ክሶች በዝርዝር ለመመለስ የሚገፋፋን ምንም ነገር የለም::

ከሁሉ መጀመሪያ ለመላ የኢትዮጵያ ተራማጆች አሳፋሪ ሆኖ ያገኘነው የምትጠቀሙበት "የክርክር" ዘዴያችሁ ነው:: ዋና ዋና ክሶቻችሁን አቀነባብረን ብናቀርባቸው፤ እንዲህ የሚሉ ናቸው:: የምትረባረቡባቸው "መሪዎች" የምትሏቸው ጓደኞች ላይ ሲሆን እነዚህ ጓደኞች ለብዙ ጊዜ አውሮፓ በመቆየት ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ስለመራቃቸው፤ የሃገር ቤቱን ንቅናቄ "ኢንፋንታይል" ብለው ስለመሳደባቸው፤ ከስህተቱም እንዲታረሙ "ኢንተርኮንቲኔንታል ማንዋል" አሳትመው ሊልኩ ስለማሰባቸው፤ አውሮፓ "ቡርዥዋ መጻሕፍት ቤት" ተቀምጠው ቲዎሪን "overemphasis" በማድረግ ለሬቮሉሽኑ ምንም "Practical Contributions" አለማድረጋቸውንና ሌላም ብዙ ብዙ ክሶችን ሠንዝራችኋል::

ይህን ሁሉ ስትሉ "Let us take their statement as a factual basis for this characterization of ours" በሳችሁ እንዲያውም "ስትጠቅሱ" ካለፋት ሁለት ዓመታት ጀምረው የሚ ወጡት "ታጠቅና ትግላችን" ናቸው ብላችኋል::

ግን እኮ እንደዚህ ማኅበራችንን /ለማሳጣት ስትነሱ እናንተ "የሳብ አ ደር ኩራትና ገበረሕብነት ባልተለየሙ ሬቮሉሽናዊ ሃቅ" /የአልጀሪያው ቡድን አነጋገር ነው፤/ ለትታገሉን የተነሳችሁት "ተራማጆች" የአዱሃሪውን የ"Ethiopian Herald" የቀደሞ አዘጋጅ የብርሃኑ ጥበቡን ያህል እንኳን ቀንነት ማሳየት አልተቻላችሁም:: ባለፋት ሁለት ዓመታት "ታጠቅና ትግ ላችን" ይህን ሁሉ ዘላበዱ ስትሉ እንዷን ከሳችሁን እንኳን ከዚህ ቦታ ከዚህ ቁጥር፣ ከዚህ ገጽ ብላችሁ አልተናገራችሁም:: አዱሃሪው "Ethiopian Herald" እንኳን ከሠስት ዓመት በፊት እንደእናንተው በማሕበራችን ላይ "ሲዘምት"

"In the wonderful world of student propaganda, there is never a moratorium on absurdity. But the silly season forslogan mongering reaches a new height in a pamphlet titled "TEGLATCHIN" (Our struggle) ..... the absurd slogans....revealed the amazing intellectual insight that prevails among the members of the Ethiopian students' Union in Europe."

ብሎ በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ሊያሳጣን ሲነሳ "መሪዎቻችን" ሳይሆን በጠቀሳሳው ማሕበራችንን፣ በደፈናው ሳይሆን ደግሞ መጽጨትቻቸንን በዚህ ዓመት በዚህ ቀን በዚህ ቁጥር በዚህ ገጽ እንዲህ አሉ እያለ ነበር:: "የሳብአደር ገብረገብነትና ሬቮሉሽናዊ ሃቅ" እያላችሁ አጉል መንጠራራቱን ተወት አርጋችሁ እስቲ የአዱሃሪውን " ETHIOPIAN HERALD " ቀንነት እና በራጡ መተማመን አሳዩን::

በተረፈ ግን የአውሮጳ ማሕበር "መሪዎች" ይህን ሁሉ የሚዘባርቁት አገራቸውን ባለማወ ቃቸው ነው በማለት አስተሳሰባቸው "betrays a stark poverity of detachment and abstraction from the realities of Ethiopia" ስትሉ፡ "ሄራልድም" ያው የኢትዮጵያን "ሪያ ሊቲስ" ባያውቁ ነው በሚል አነጋገር " It would ofcourse be asking too much of Ethiopian students here and abroad to know their country with some degree of accumcy" ብሎ ያሾሟጥጣል:: የሐገራቸንን ሁኔታ የማናውቅበት ዋናው ምክንያት ሲቆርብ ለን ደግሞ ሁለታችሁም ያው አንድ አይ ያልኅና የሰለቸንን ምክንያት ስትሰጡን እናንተ "Indeed a product of their host invironment in which they have drooled for ten to fifteen years..."

ስትሉን "ሄራልድ" ደግሞ የዚህ ሁሉ "ሪያሊቲስ" መሳት ምንጩ እነዚህ የአውሮጳ ማሕበር ሰዎች " ....Ethiopian scholars footloose and fancy free in Europe"

በመሆናቸው ነው ብሎን ቁጭ ይላል::

መጀመሪያ ነገር በመጠሪያ ስሙ "በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር" ተብሎ የተሰየመ ድርጅት አባሎችና መሪዎች "ከኢትዮጵያ ርቀው መገኘታቸው" ለአዱሃሪውም ሆነ "ተራማጅ ነኝ" ለሚለው ይህን ያህል ገራ ያጋባበት ጉዳይ አልገባንም:: ታዲያ የት ይሁኑ?

ሁለተኛ ነገር የሃገርን "ሪያሊቲስ" በሚገባ ማለወቅ ና በጆስገራፊ አቀማመጥ የግዱ አንዱ ዓይነት ግንኙነት ካልፈጠርን ብላችሁ አኝኝ ካላችሁ የምትቀልጡት እናንተው ናችሁ፡ በዚህ በአዲሱ "ሬቮሉሽናዊ" አስተሳሰብ ከጨዱን በሱዳን የሚገኙ ጓደቻችን "ዝም ብሉ እና ብቻ እንናገራለን፣" ቢሉን ምን ልንመልስ ነዉ?

አይደለም "ጓደቻች" እና ለምሳሌ እናንተን የሃገራችሁን "ሪያሊቲስ" አታውቁም ብለን

ብንላችሁ መደባዊ ምንጫሁን ተመልክተን ሌኒን እንዳለው: "It all adds up to that petty bourgeois diffusivness and instability; that incapacity for sustained effort ............" 3

በማለት ትንፍናችሁንና ቁንጥንነታችሁን ለማመልከት ነው እንጂ ከኢትዮጵያ በመራቃችሁ አይደለም::

የሆነው ሆኖ የኒትዮጵያን "ሪያሊቲስ" አወቀንም አላወቀንም የኢትዮጵያን ተማሪዎች ንቅናቄ "በሚያሳየው ደገንገትና ቁራጥነት ላይ ለሪቮሉሽናዊ ተፃሪ ተገቢ ቦታውን እንዲሰጠው አሳስበን እንጂ በመጽሔቶቻችን ላይ "ኢንፋንታይል" ያልገበት ጊዜና "ኢንቱርከንቲነንታል ማንዋል" ይላከለት ያልነበተ ጊዜ የለም:: እናንተ ግብ ብላችኋል::

"It is precisely because of its essentialy spontaneous disorderly and infantile nature that the movement remained exposed and defenselless during the three months propaganda just before the decmber massacre..."4

ይህንን <u>እናንተ</u> ሳትሆኑ እኛ ብለነዉ ቢሆን ኖሮስ? "የአውሮጳ መሪዎች" አልፈው ተርፈው "ለታህሣሡ ፋሺስታዊ እልቂት ዋናዉ ተጠያቂ ፋሽስቱ መንግሥት ሳይሆን "precisely because2 ንቅናቄውን"disordery and infantile" ያደረጉት የተማሪዎቹ ጥፋት ነዉ" አሉ ብላችሁ ትተረጉሙልን እንደነበረ ግልጽ ነዉ*: እኛ ግን አናደርገው:: ስለዚህ የሃገር ቤቱን ንቅናቄ ስደባችሁ ብለን "ህንዱ ቡክ ኦንሪቮልሽን" በሚል አርእስት "Teach Yourself revolution በሚል መልክ "ሪቮሉሽኑን በቀላሉ የሚያስረዳ" የኪስ መጽሐፍ አውጥታችሁ "ተራማጅ የሆነክ ሁሉ ይኸ ይገባህ በቃልህም ያዘዉ" ብላችሁ አምና ሃበተናችሁት እናንተ ናችሁ እንጂ እኛ አይደለንም::

ግን ደግመ ይህንን ስላልን ከሃገር ቤቱ ንቅናቄ ጋር ለጋራ ትግላችን በጠበቀ ሽመተሳሰብ መንፈስ አንሠራም ማለት አይደለም:: እንሠራለን:: ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምረዉ ይሳደቡ ነበር የተባሊት መጽሔቶቻችንን ብታዩዋቸው ስለ ሃገር ቤቱ ንቅናቄ በተነሳ ቁጥር በወገናችን ላይ የሚደረገው ፋሺስታዊ ግፍ ለማጋለጥ ትግላቸውን ለማስተጋባት ከዚያው <u>ከጓደኞቹ ተማሪዎች</u> የሚደርሱንን ጽሑፎች ቀድሚያ እየሰጠን እናወጣለን እንጂ "እንደማንሳደብ" ትረገላችሁ፣ የቱፃሪ መጻሕፍትንና ሪቮሉሽናዊ ሊትሬቸርን ለማስገባት የምናደርገዉ ጥረት ለእናንተ"የቱፃሪ ሚና ማገነን መስሎአችኋል:: እንዲያውም ይህ የኛ ቱፃሪን "አብርሊምፋሳይዝ" ማደረግ "ለታጋልጡ ከተነሳችሁበት "ክስ" አንዱ ነው::

በዚሁ "ሳም ቱውስት..." እንደዚሁም ደግሞ በቡሊቲናችሁ ቁጥር 6 ላይ እንኳን " Petty bourgeois philistines in the bourgeois liveraries"of Europe" Practical Contribution

የማያደርጉ የፍቺ ሪቮሉሽናዊያን እያላችሁ ትወርፉናላችሁ መቼም "ቡርዦዋ መጻሕፍት ቤቶች" ለተባለው፣ የምዕራብ አውሮጳ መጻሕፍት ቤቶች ገና "ቡርዦዋ" በመሆናቸው እኛ እናንተን ይቀርታ የምንጠይቀበት ጉዳይ የለንም:: ግን እናንተ መጻሕፍት ቤት ስትገቡ አንዱ አንዱ ሪቮሉሽናዊ ስድቦች ነጠቅ ነጠቅ አድርጉ ለመዉጣት እንጂ በቁም ነገር ዕዉቀት የምትገበዩ አትመስሉም:: እንደዚህም ስለሆነ የቱፃሪ ማጋኑኑ ክስ እስከዚህም ማኅበራችንን ለመሳደብ ሳይሆን የናንተን ስንፍናም ለመሸፈን የተወረወረ ይመስላል:: ስለሆነም የማርክሲዝምን ሀሁ እንኳን ሳታዉቁ ለሪቮሊሽኑ "ፕራክቲካል ኮንትሪቡዩሽንስ" ለማድረግ ሲሆን ምን ያህል <u>እንደምትጋናበሩ</u> ዝቀ ብለን "ሳይንሳዊ ትንተናችሁ" ዉስጥ ገብተን ስንዳክርበት እናየዋለን:: እዚህ ላይ ግን ታላቂ ሌኒን "በአዉሮጳ ቡርዦዋ መጻሕፍት ቤቶች" ቁጭ ብሎ ስለ ቱፃሪና ቱፃሪን ስለሚያንቋሽሹት እንደእናንተ "ፕራክቲካል" ሰዎች ምን ይል እንደነበረ አስታዉሰናችሁ እንለፍ::_

* ተገብ የንም አልቀረን:: ይህ ጽሁፍ በተጻፈ በሁለት ሳምንት ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን የተባለው የአድርባይ ግለሰቦች"ንቅናቄ"ክ ተደረገበት ጊዜ ይህ ክስ ቀረበ:: ማህበራችን ለዚህ መሠረተቢስ ክስ የሰጠውን ማብራሪያ ከዚህ ጥናት ጋር እናያይዘዋለን::

" Those people who cannot pronounce the word "theorietician" without a sneer, who describe their genuflecations to common lack of training and backwardness as a "sense for the realities of life" reveal in practice a failure to understand out most imperative Practical tasks....... if, besides this, these amaterurs are enamored of their primitive methods and insist on writing the word "practical in italics," then they are hopeless amature and, of course, certainly can not INGENERAL COPE WITH ANY POLITICAL TASKS." 5

ለዚህ ነው እናንተም ከሁለት ያጣ ጎመን ሆናችሁ ስትደናበሩ በቲዎሪውም ሆነ በሥራ በማኅበራችን ላይ የረባ ሂስ ማምጣት ቢቸገራችሁ በየትኛውም የፖለቲካ መስመር ልዩነቶቻችን ላይ ቁሞ መከራከር አቅታችሁ ነገሩን ሁሉ "የመሪዎች" ጉዳይ የምታደርጉት::

ግን እኮ ይህ "መሪዎች፣ መሪዎች" የሚባለው ፈሊጣችሁ ሁሉ ወጥመድ ነው:: ሙከራችሁ ክርክሩን በግለሰቦች ላይ አድርጉ ሰው በፖለቲካ ጉዳይ እንዳይከራከር ለማድረግ ነው:: ወጥመዳችሁ ውስጥ አንገባም:: የግድ ጉትተን የፖለቲካ ክርክር ውስጥ እናስገባችኋለን:: የፖለቲካ መስመርን ቀይሶ መከራከር ሲያቅታችሁ "መሪዎች መሪዎች" እያሉ መጮህና በዚህም "ተከታይን" ሁሉ <u>እንደበግ የሚነዳ እንጂ አመዛዛኝና መምረጥ የማይችል:</u> ነገር አስመስሎ ማቅረብ ዛሬ አልተጀመረም:: ሌኒን በዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላል::

"These people want to INVENT something quite out of the ordinary, and; in their effort to be clever, make themselves ridiculous.....one can only see simply a thoughtless and incoherent use of the now "fashionable" terms! "masses" and "leaders", Theseépeople have heard and memoraized a great many attacks on "leaders", in which the latter have been contrasted with the"masses"; however they have proved unable to think matters put and gain a clear understanding of what it was all about". 6

ማኅበራችንን ከፖርቲ አነፃፀራችሁ ብንባል ይህ ጥቅስ በትግል ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ክስ አዲስ እንዳይደለ ያስረዳል ብለን እናምናለን:: እነዚህ የኛ <u>ተራማጅ መሳዮች</u> ትንሽ ብትለዩ "የሰማችኋቸውንና በቃል" ያጠናችኋቸውን ክሶችና ስድቦች" ሁሉ በጅምላ እየወረወራችሁ ብዙውን ጊዜ የገዛ ስድቦቻችሁ እርስ በእርስ እየተጣፉ ተከሳሽን"ነፃ" የሚያወጡ ስለሆነ ከሌሎች ይልቅ አስቂኝ ስለሆናችሁ ነው:: እንግዲህ ወደ ፖለቲካ "መስመራችሁ" እንገባ::

1. <u>ተስፋ የቆረጠው ማን ነው</u>?

በናንተ አስተሳሰብ የፖለቲካ መስመር ልዩነትና ትግል በንቅናቄያችን ውስጥ የተጀመረው ከታህሣሥ እልቂት ወዲህ ሲሆን ጠሩ "ተንበቀቡቀውና ተስፋ ቆርጠው "ትግሉን በተውት" ሶያችና ከዚህ እልቂት "ሪቮሉሽናዊ ትምህርት ቀስመው" ለትግሉ ጠንክረው በወጡት ወገኖች መሃከል ነው::

"Eversence the massacre of december 1969, two basic trends have been manifested in the Ethiopian student movement. The forces that summed up experience of the revolutionary student movement on the one hand, and the forces that lost hope in struggle and adopted the attitude of passivity and the philosphy of resignation of the other. The two trends have been locked in fierce struggle in the Ethiopian student unions abroad for quite sometime."7

ጥሩ ነው:: ተስፋ መቁረጥ ካነሳችሁ ስለተስፋ መቁረጥ እናውራ:: ግን ካሁኑ እርስ በርስ እየተቃረናችሁና ክሳችሁን እያጣፋችሁት መሳቂያ አትሁኑ:: መጀመሪያ ነገር ትንሽ የሚመስል ነገር አውሩ:: ሁለተኛ ነገር ደግሞ የግድ "ለትግሉ ሲባል" እርስ በእርስ የሚቃረኑ ቅጥፈቶች ለማውራት ከተገደዳችሁና ቢያንስ አሁን "ሞቷል ያላችሁትን ሰው" ቁሞ ሲሄድ እየነው"

ለማለት ለአንባቢ ትንሽ ፋታ ስጠት:: እንዴት ገጽ እንኳን ፈቀቅ በሉለት:: በዚህ ጥቅሳ ቹሁ እንደምናየው ግን ከመስመር መስመር ሲሆን መሳቂያ ተሆናላችሁ::

በእናንተ አባባል ከሆነ ከኃህሣሡ አልቂት በኋላ "ጉበዝ፣ ጉበዞች" /ማለት እናንተ/ በአንድ በኩል፣ ተሰፋ ቆርጠን ፍልስፍናችንን "አርፍ መቀመጥ ይሻላል" ብለን ተለመን ትግሉን አርግፍ አድርገን ትተን ያለነው እኛ በሌላ በኩል ተሰልፈናል ማለት ነው:: ባጭሩ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ /በውጭ አገር/ የኢት. ተ. ንቅናቄ በነሙትና ከሙታን በሚቆጠሩት መሃከል ከሁለት ተከፈለ:: ግን ታዲያ የምንይዘው የምንለቀው ግራ የሚገባንና "ከምትንበት" በዱንጋጤ የምንባንነዉ ወዲያው አስታትላችሁ "በውጭ አገር በሚገኙት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ውስጥ ሁለት ወገኖች አሉ? አስቃቂና ኃይለኛ በሆነ ትግል ቢ.ተና ነቁ ጥቂት ጊዜ አልፍአቸዋል" በትሉን ነው:: ታዲያ እንዲህ በሆነ "የሙታውን" የአውሮጳ ማኅበር እናንተ "የቆማጥ ሁት" አም [illegible] ሁ መጣል ያቃ.ተሁ "ከሰ[illegible] አይበ[illegible]ል ደማ" መሆናችሁ ይሆን? ነዉ ወይስ "ደርን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት" እንደሚባለው "አስቃቂ ትግል[illegible] ስንትና ነቀ የምትሉን እ,ሃን ከሙታን የምት ቆጥሯንን ወገኖቻችሁን ስትደልሉን ነው?::

በዉነቱ ስለማኅበራችን ተስፋ መቁረጥና "እጅ አጥፍ መቀመጥ" ከዚህ አልፈን ብዙም ጭቅጭቅ ባላስፈለገ ነበር:: ግን ደግመ በማኅበራችን ውስጥ ሁሉ የሚያውቃቸውን አንዳንድ የሚሠሩና የሚጻፉትን ነገሮች እየጠቀስን ተስፋ የቆረጥ ነዉ እኛ እንዳልሆንንና <u>እነዚህ "ጉደኞች"እንደሆኑ</u> ማሳየት አለብን::

ምክንያቱም ለኛ ተስፋ መቁረጥ ማለት ነገር ዓለሙን ትቶ እጅ አጥፍ መቀመጥ ብቻ አይደለም:: ሌላ ዓይነት ተስፋ መቁረጥ አለ:: መሸበር፣ አለቅጥ ማወላወል፣ መፈርጠጥ፣ ተስፋቢስነት በገፈፋው ቸኩልነት መንቆራጠጥ፣ ይህ ሁሉ አንዱ የተስፋ መቁረጥ ምልክት ነው:: እንዲያውም ልዩነት የተጀመረው እኛ ተስፋ ቆርጠን "አንታገልም" በማለታችን ሳይሆን እናንተ ተስፋ ቆርጣችሁ <u>ከሁን ወዲያ ያለመሣሪያ ትግል ሌላው ሁሉ ከንቱ ነው</u>: እያላችሁ መደንፋት ስትጀምሩ ነው:: እዛቸው ጉዳይ ላይ እንኳ ልብ ብለን ብናይ ለዘላቂው ትግል ሲባል በወጉ መከራከሩን ትታችሁ በስድብ ጋጋታ ብቻ ሰው ለማደናገርና ሥ[illegible]ያዊ ዱላን "ለመጉናፀፍ" እንዴት እንደምትጥሩ ለማሳየት ይቻላል::

"These people have heard and memorize a great many attacks ......."

እንደተባለው እናንተም በቃል ያጠናችኋቸውን ስድቦች ስታዘንቡ ግራ ቀኝ እንኳን አትመለከቱም:: በናንተ አስተያየት ስደብ ከሆነ፣ የቃሉ አጣጣል: ደስ ካለ፣ <u>ውዝንበር ነዝቶ ጊዜያዊ ምስኪን ዱላ "ካጉናፀፈ"</u> እንኳን እውነት ይሁን ውሸት ልትጨነቁበት ይቀርና እርስ በእርሱም ቢቃረን ግድ የላችሁ:: ይህ መቸስ በጽሁፋችሁ ውስጥ ደጋግመን የምናየው ነገር ሆኖ እዚህ ላይ ግን ዓይን ያወጣል:: "እጅ አጥፍ መቀመጥ" ትግሉን አርግፍ አርጉ መተዉ" እያላችሁ ያዝነባችሁትን ክስ አንባቢ ገና አዋህዶ ሳይጨርሰው እኛም "ተስፋ የቆረጣችሁት እናንተ ናችሁ" ብለን ለመመለስ ስንዘጋጅ ሁለት ገጽ ሄዱ ብላችሁ እፀንተ /::/እኛን/::/ ገጽ 32 ላይ "the comp of the desperados :" ብላችሁ ትቀደሙናላችሁ::

"ዲስፔራደስ" ምን ማለት ነዉ? "Person ready to do any reckless act" ማለት ነዉ:: ጊዜያዊ ድርጊት በዘላቂ ዓላማ ላይ የሚያመጣውን ውጤት ሳያይ ጽንደ እሳት እራት የሚጋበዝ፣ ትዕግሥት ከማጣትና ከቸኩልነት የተነሳ እንደበሽታ የሚከጅለውንና የሚሠራውን የማያውቅ ሰው ማለት ነው:: ቃሉ ትርጉሙ እንግዲህ እንዲህ ከሆነ በእናንተ በኩል ሌላ

ተራማጅ ቃል ካሳመጣችሁ እና "የፍቴ ሪቮሉሽናውያን" ተስፋ ቆርጠን እጅ አጥፈን የተቀመጥ ንና እንዲያውም ከዚቸው ቃል ቀጠል አድርጋችሁ በአውሮጳ ተመቻቸተው የተቀመጡ "ኢንቴሌክቱዋል ቱሪስትስ" የምንባል ሰዎች በምን ፈሊጥ "ዲስፔራደስ" ልንባል እንደምንችል ፈጽሞ ገራ ገብቶናል::

ስደብ ስትለጥፉ "የሴንትራል ኮሚቴ" አባል የሆነ ሁሉ በአውሮጳ ማኅበር ላይ አንድ ስደብ ያሳወጣ የማርያም ጠላት እየተባባላችሁ ነው መሰል፣ እንደዚህ በነፍስ ወከፍ የምታወጡ ዋቸውን ስድቦች የእያንዳንዱን "መሪ" መብት ለማክበር "ያለሳንሱር" ታወጧቸዋላችሁ መሰል? ጽሑፋችሁ በእንዲህ ዓይነቶች መሠረተቢስ ጥቅሶች የተሞላ ስለሆን በየጊዜው እነሱን እናቅ ና እያልን የኛንም ያንባቢንም ጊዜ አንፍጅም:: ስለዚህ ይህን ትተን ይልቁንስ በኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት ተስፋ እንደቆረጣችሁና እንዴት የተሳሳተ የፖለቲካ መስመር እንደያዛችሁ እንመለከት::

የኛን ተስፋ መቁረጥ "የምታስጀምሩን" ከታህሣሥ አልቂት በኋላ ነው:: በዚያን ጊዜ እና "የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ" "ቡቃያ ከንፍ" /ፖንኪ ሳትራተም/ መደናገጣችን በከንቱ ብቻ ሳይሆን እናንተ "ጉበዞቹ" በዚህ አልቂት ያልተረበሻችሁና እንዲያውም በሬቮሉሽናዊ መንፈስ ተመርታችሁ ትልቅ ትምህርት "እንደቀሰማችሁ" ትነግሩናላችሁ::

"A movement under the pressure of repression might seem to slip backwords while in fact it is moving forward. When the enemy who uses duely a tactic of "benevolence and "vertue" is forced to show its essentiel facist nature, that is not a light matter to be dismissed with slight facination. The self exposure of the regime that it would go any lengh to kill students was an important lesson to the Ethiopian people: እንዲያውም "For revolutionaries who have understood the depth of the problem in out country,......this phenomenon can only be taken as a signal to continue agitation and propaganda in new form and conditions....Revolutionaries always must anticipate the worst from their enemis, no revolutionary is woth of the name if he or she anticipates mercy from the enemy." 8

ጉዳዮች ማለፊያ ብሳችኋል ግሩም ነው:: ግን ሁለት ነገሮችን እናስታውሳችኋለን:: አንደኛ ነገር ይህ ሁሉ ማኅበራችን ዛሬ ሳይሆን—የዛሬ ፬ራት ዓመት "ተስፋ ቆርጦ ሲንቦቀቦቅ" ይለው የነበረው ጉዳይ ነው:: በ1963 ዓ.ም. "ለወጣት ሰማዕታት መታሰቢያ ቀን" ያወጣውን መግለጫ መለስ ብላችሁ ብታዩት ይበቃል:: በዚህ ድርጊቱ መንግሥቱ ፋሺስታዊ መልኩን እንዲያሳይ ተገደደ ነው የምትሉት? የአውሮጳ ማኅበር መግለጫ በዚያን ጊዜ እንዲህ ይል ነበር::

"በዛሬዩቱ ኢትዮጵያ እንደታህሣሡ ቀን በየዐለቱ በያለበት ንፁህ ኢትዮጵያውያን ይጨፈጨፋሉ:: መንደሮች ይጠፋሉ:: ቤተሰብ ይበተናል:: ንብረት ይፈታል:: ሕዝባችን በፋሽስታዊ ግፍ ይቀረጻል:: ይጋዛል:: ይሰቃያል:: ይህንን የወጣት ሰማዕታት መታሰቢያ ቀን ታሪካዊ ከሚያደርጉት ጉዳዮች አንዱ ይህ መንግሥት በአፈጻጸሙ ፕሮፖጋንዳው የሚሸፍነውን የግፍ ድርጊት በዓለም ፊት በግልጽ በመፈጸም በዚያች ቀን በእውነተኛ ፋሺስታዊ መልኩ እንዲጋለጥ መገደዱ ነው::" ካለ በኋላ በዚህ መግለጫ ላይ ይህ ራሱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ትምህርት እንደሆነ ያስገነዘባል::

ከጠላት ምንም ዓይነት ምሕረት መጠበቅ የለብንም፤ ለማንኛውም ነገር መሰዋዓት አለብን ነው የምትሉት? የማኅበራችንም መግለጫ የዚያን ጊዜ "የመንግሥቱን ፋሺስታዊ ጠባይና የኢምፔሪያሊስቶችን አጥፊ ምክርና ድርጊት በሌሎች ሕዝቦች ላይ /በሀገራችንም ላይ/ የሚያደርገውን በደል ስለምናውቅ ይሄ ድርጊት ከሰማይ ዱብ አላለብንም" ይል ነበር::

ከዚያም በኢትዮጵያ ሕዝብ ፈጽመን ተስፋ ያልቆረጥንና የወገኖቻችንን መስዋዕትነት ትግሉን ለመጠቀል እንጂ "እርግፍ አርጉ" ለመተው እንደማይገፋፋን ሲያስረዳ:- ይኸው መግለጫ በትግላቸውና በመስዋዕትነታቸው አርአያነት ትግሉን የምንቀጥለው የኢትዮጵያ ወጣቶች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተዋህደንና ገፈኞችን ደምስሰን እኪስሥርዓት ስንመሠርት ለፈሰሰው ደማቸው ግምት የማይገኝለት ዋጋ እንሰጠዋለን::" ብሎ ነበር::/ሰረዝ የተጨመረ/

ባጭሩ እንግዲህ እናንተ ዛሬ የታህሣሥ ግፍ በተፈጸመ በአምስት ዓመት የተገለጠላችሁን "ምስጢር" ማኅበራችን ቀደም አድርጎ ቀስሞት እንደነበረ ግልጽ ነው:: የት ላይ ነው ታዲያ "አይ የኛ ነገር አለቀ ደቀቀ የኢትዮጵያ ገዢ መደብ ፈጽሞ የማይበገር ኃይለኛ ነው፤ ትግሉ ይብቃን" ያልነዉ? የት ላይስ ነው አንዳንዱ መናኛ "ዲስፔራዶስ" በሕዝቡ የማይበገር ኃይል ተስፋ ቆርጠን "መሣሪያ ያስስታጥቀን እንበለው፤ እንፈርጥጥ" ያልነዉ?? እረ ለመሆኑ እናንተስ የዚያን ጊዜ "የቀሰማችሁት ረቮሉሽናዊ" ትምህርት" ምን ምን አሳብ ያስጮሃችሁ ነበር?

ግልጽ ነዉ የዚያን ጊዜ እናንተ በሰፊዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ ቆርጣችሁ መዱኀኑም የናንተ መሣሪያ አንስተ ዉርዉር ማለት መስሏችሁ ሌላዉ ቀርቶ የተማሪዉ ንቅናቄ እንኳን ትጥቅ ከሌለዉ ዋጋ የለዉም ትሉ ነበር:-

"The guns that roared in december 1969 in defence of feudofascism and imperialism must be recognised as the baptism by fire of the emergent Ethiopian revolution....we cannot think any more of the Thiopian revolution within the framework of an unaremed student movement." /emphasis added/

ታዲያስ በፋሺስታዊ ድርጊቱ የኢትዮጵያ መንግሥት የማይበገር ኃይለኛነቱ እንጂ "በዓለም ፊት" ደካማነቱን እንደገለጸ ለናንተ መቼ ታያችሁ? ቃጠሎው ጎነሳ መፋጀቱ አስደነገጣችሁ እንጂ የሚሰጠውን ብርሃን መቼ ልብ አሳቻሁት? ረቮሉሽናዊ ትምህርተ ቀሰምን" የምትሉትን ለሌላ አድርጉት:

ታዲያ አንባቢ: የትኛው ነው "ዲስፔራዶስ"? ከዚያ በኋላስ በተማሪያች ንቅናቄ ውስጥ የተፈጠረው ውዝግብ በዚሁ እናንተ "መሣሪያ አምጡ እንፈርጥጥ" ስትሉ ማኅበራችን ደግሞ ለማይቀረው ሕዝባዊ አመጽ እንደራጅና ሕዝቡን እናደራጀው ስንል አይደለም እንዴ ክርክሩ ሁሉ የተነሳው?

አዎን፤ ስለጦሩ ትግል ደግሞ እናውራ፤ በዚያን ጊዜ "አሁኑኑ ጦርነት መጀመር አለብን" እያላችሁ ስትወሸክቱ እንደነበረ ማንም የሚያውቀው ነው:: ማኅበራችን የሕዝባዊ አመፅን አስፈላጊነት ሳይክድ የነቃና የተደራጀ ሕዝብ አመፅ እንጂ የናንተ ውርውር ምንም ፋይዳ እንዴሌለው ለማስረዳት ሞከረ:: እንደዚህም የተቃወሟችሁን ተራማጆችና አገር ወዳዶች ሁሉ ከክህደት ቆጥራችሁባቸው እንደሚከተለው መደንፋት ጀመራችሁ::

"The armed strugglw cannot be postponed indefinitely or until a powerful, mature and disciplined party is created; it is not necessary that the party should have thousands or even hundrads of member: before it

IHitiales armed strugglw. To wait until such a party is created would be treasson..........." 11 (emphasis added)

እንግዲህ በተማሪም ንቅናቄ ውስጥ የተነሱት ልዩነቶች እናንተ ለዚህ አጣዳፊ "የጦር ትግል" "ቆራጥ ቆራጠቾን" ለማነፅ እንጠቀምበት ስትሉ እኛ ደግሞ ተግባራችን በልዩ ልዩ ጊዜያዊ ጥያቄዎች ላይ እየተመረኰዘን ሰፊ ፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔሪያሊስት ፕሮፖጋንዳና አጂቴሽን ማድረግ ያስፈልጋል፤ ንቅናቄያችን መስፋት አለበት ስንል ነው:: ይህን የኛን አቋም አብዛኛው ተማሪ ቢቀበለው፣ በተለመደ አድር ባይ አንደበታችሁ ይህንን ተግባር እኛም እናምንበታለን እያላችሁ ታወሩ ጀመረ:: ነገር ግን በምታደርጉት ልዩ ልዩ ፀረ ዲሞክራቲክ ተግባርም ሆነ በምታወጧቸው መጽሔቶች ምንም ዓይነት የሰፊ ዲሞክራቲክ ንቅናቄ መልክ ባለማሳየታችሁ ይህ አቋም ከአንገት በላይ ብቻ እንደ ተቀበላችሁት ተነቃባችሁ:: ቢሆንም የሌባ አይነ ደረቅ መልሶ ለብ ያደርቅ ነውና ጭራሹን ነገሩን ሁሉ አገላብጣችሁ እናንተ/:/እኛን /55/ "የተጣላና ቸው የተማሪውን ንቅናቄ ለማጥበብ ስለሚሞክሩና በማኅበራት ውስጥ ዲሞክራሲ ስለጠፋ ነው" እያላችሁ አዲስ "የትግል ምዕራፍ" ከፈታችሁ:: ነገርም ለማሳመር ተቀባይነት ያጣውን ፍኮይዝማችሁን አሳየንም አለስማንም ጠሻችሁ ተሰደብን፣ ተደፈርን ትሉ ጀመር:: በዚች "ሳምቱውትስ..." ጽሑፋችሁ ላይ እንኳን "አሁንም ፍኮይስት እያሉ ይሰድቡናል" ተሳሳችሁ::

መጀመሪያ ከዚህ ገፊት ለምን "ፍኮይስት" እንዳልናችሁ እናስረዳ:: በኋላ ደግሞ "<u>አሁንም</u>" ለምን ፍኮይስ ልንላችሁ እንደምንችል እንመለከታለን::

መቼም ፍኮይስት ማለት ሰው የሚበላ ጭራቅ መስሏችሁ እንደሆነ አይዟችሁ:: እኛ ፍኮይስት ያልናቸው የምትጸፋትንና የምታወሩትን ሌሎች <u>ፍኮይስት ነን የሚሉ ሰዎች</u> ጋር አየመሳሰለነው ነዉ እንጂ ከመሬት ተነስተን አይደለም::

የፍኮይዝም ዋና ፍቺው ጥቂት መሣሪያ የያዙ ቡድኖችን /አርባና ሃምሳ ሰዎች ይላቸዋል ሬጂስ ደብሬ/ በባላገር ዉስጥ እየተዘዋወሩ በያለበት የጦር ትግል ጉጅ /ፍኮ/ በማቀጣጠል ሕዝቡን በማነሳሳት ሬቮሉሽኑን ከግቡ ሊያደርሱት ይችላሉ የሚል ቲዎሪ ነው:: እንደዚህም ስለሆነ የጦር ትግሉን ለመጀመር የሕዝቡ የንቃት ደረጃም ሆነ የመደራጀት ጉዳይ እስከዚህም መሟላት አያስፈልገውም:: እንዲያውም ይህ ንቃትና መደራጀት <u>በጦፏ ትግል ውስጥ እየተሟላ ይሄዳል</u> የሚል አቋም አለው:: በፍኮይስቶች ዕምነት ሳንረጂስ ደብሬ:—

"It is not always necessary to wait for a revolutionary situation to arrive, this can be created by a revolutionary focus"

ስለሚሉ ሕዝቡን የማደራጀቱን ተግባር ይንቁታል::

ታዲያ እነሱ "አርባና አምሳ ሰዎች የያዘ ቡድን" የሚሉት እናንተ "ሚነምም ፖለቲካ ፖርቲ" ብላችሁ ከምትጠሩትና ይህ ፓርቲ "በመቶ የሚቆጠሩ አባላት እንኳን" አያስፈልጉትም ካላችሁት ጋር ተመሳሰለብን:: እነሱ ነገሩ ሁሉ በሬቮሉሽናዊ "ፍኮ" ይሟላል ሲሉ እናንተ, ካላችሁት ጋር አንድ ሆነብን:: ከዚህ ሁሉ አልፋችሁ ከኛ "ከቦቀቧቆች"ለመቀራረጥና በሚይዙትና ገና ባላስለመዳችሁን ዱንፋታ

"We say 'basta' to phIlistine cowardice and halfheartedness, we say 'basta' to petty bourgeois defeatism and opportunism, We recoggize that theris only one way to liberation and that is revolutionary violence. We belive there is only one way to get that and this is revolutionary

organisation. Seize the time! And seize the gun! Long live the Ethiopian Revɔlution!" 13

እያሳቻሁ ስትጭሩና ስትጮጪጭሩ /ሪቮሉሽናዊ ድርጅት ስትሉ የሕዝብ ድርጅት ሳይሆን" በመቶ የማትቆጠሩት" ጀበኖች ቡድን መሆኑን ከፍ ብሳቻሁ ነገራቹሁናልና/ እንደዚህ "ጉበዝ፣ ጊዜው አያምልጥህ፣ በረትህን እንሰ፣ እያለ ከፍኩ ይዝሙም አልፎ ወደፋከራ የሚከጅለው አነጋገራችሁ ዛሬ ቢያስቀን የዚያን ጊዜ አሳሳቀንም:: ገና እናዉቃቹሁም ነበርና::

ታዲያ "ጋደች" ይህን ሁሉ አመሳስለን፣ ምንም ጠንቋይ ሳንቀልብ ነገሩ ተገልጦልን "ፍከይስጬ" አልናችሁ:: በዚህም ልንታገሳችሁና መሥመራችሁን ለማጋለጥ ተነሳን:: በኋላ ግን በተረጋጋው ሁኔታ የናንተ "ህዝባዊ ጠር" ተቀባይነት ሲያጣ እያቻሁና የጊዜውን ርጋታ ትዕግሥት የሚጠይቀውን ተግባር ትታቹሁ በሌላ አቀጣጫ ደግሞ ዉዥንብር ለመንዛት ታነፈንፋ ጀመር:: እኛም እንደዚህ እንደ ገሃነም እሳት የሚያገላቻሁ እንደ ገሃነም በረዶ የሚቆቀዘቅዛችሁ የንዑስ ከበርቴ መደባዊ መሠረታቹሁ ስለሆነና ሌኒንም እንዳለዉ አጉል ድንፋታ የሚያጠቃው ንዑስ ከበርቴ ምንጊዜም ቢሆን:

".....easily goes to revolutionary extremes but is imeapable of perseverance, organization, descipline and stead fastness"

ያለውን በመገንዘብ በፍጹም አልተደነቀንባቹሁም:: እንዲያውም እንደኛ/በመጭው ሪቮሉሽን ንዑስ ከበርቴው ምንም ወላዋይነት ቢያጠቃውም እስከ ፡ውስነ ደረጃ ድረስ በአጋዥነት ሊሰለፍ ይችላል በሚል እምነት:

ሁለተኛ/ መቼም ሰፊ ንቅናቄ ሲባል ሁሉን ሰብሳቢ ዱር ነዉና እናንተም ከነጉድላታችሁ ገብታቹሁ መሳተፋችሁ ዲሞክራሲያዊ መብታቹሁ ነው በማለት እየደጋገምን የአንድነት ጥሪ አደረግንላቹሁ::

በመሃል ታዲያ የፈለጋቹሁት አቋም/ፍከይዝም/ እንደማያዋጣ በመገንዘባቹሁና እንዲያዉም ትገሉ "ረዥም ጉዞ" ነው ስትባሉ ያው "የለየለትን መዋሃድ" ሰትጠብቁ መንገዱ ረዘመ:: ሌላ ዐይነት ተስፋ መቁረጥ አመጣችሁ:: ይኸውም ደግሞ "ድራማ" መፍጠርን የሚወድ፣ ልታይ ልታይ ማለት የሚያጠቃው፣ ዉዥንብር ሲፈጠር ውሃ እንደገባች ዓሣ አካባቢው የሚዋሃደው፣ የአናርኪ ዝንባሌ ሆነ:: አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው እንደሚባለው በየጊዜው እናንተው አንድ "ክስ ታነሱና ስመለስላችሁ ቆሞ መከራከርን እንኳን ከትልቅ ነገር ቆጠራችሁት:: ስለዚህም እንደዚሁ ከአንዱ መሠረተቢስ ክስ ወደሌላው መሠረተቢስ ክስ እየተንዩራጠጣችሁ ጾጽጸቱ××ጰጸ ጸሄጐ በአንዲም ክሳችሁ ላይ ቅማችሁ ሳትከራከሩ እዚህም እዚያም "የከርከር" ጉጆ /ፍከ/ እያቀጣጠላቹሁ የናንተ ነገር በዚሁ ይወጣላቹሁ ጀመር:: በዚህም በጀመራችሁት አናርኪ በማኅበሮቻችን ዉስጥ አንድነትን ለማደፍረስ መጣራችሁን በመገንዘብ አምና ጠቀሳሳ ጉባዔያችን ይህን ፀረ ሪቮሊሽናዊ ተግባራቹሁን እንዲታቆሙ ጠየቃቹሁ:: ግን አሁንም ቢሆን ያ ፍከይዝማችሁ ተጻፍኖ አዲስ አናርኪያችሁ ሲስፋፋ ማኅበራችን ይዚህን ድርጊታቹሁን የመደብ ይዘት ፈጽሞ አልሳተውም ነበር:: በንዑስ ከበርቴያች ዓለም "ረዥሙን ጉዞ" ገና ቆጭ ብለው ሲያስቡት ተስፋ መቁረጥና በአካባቢው ዉዥንብር እየነዙ መዋኘት የተጀመረው ዛሬ አይደለም:: ሌኒን ስለእንደዚህ ዓይነት ተስፋ መቁረጥ ደግመ እንዲህ ይሳል::

"Certain people who were inattentive to the conditions for preparing and developing the mass struggle were driven to despair and to anarchism by the lengthy delays in the decisive stnuggle......." 14 ግን ደግሞ ያ የተጻፈውን "ፍከይዝም" ለማረሳሳት በዚህ ጽሑፋችሁ ላይ "any movement is bound to make left errors and excess": ብላችሁ የጻፋችሁት ገና ቀለሙ እንኳን ሳይደርቅላችሁ "ፌዴሬሽናችሁ" ደግሞ እንደገና "በስተግራ" ፈርጥጦ ቀደማችሁ:: "የምን ፖርቲያች ነው፣ የምን ድርጅት ነው፣ ጊዜው የሕዝባዊ ጦር ጊዜ ነው፣ ጉበዝ "seize the time!seize gun! እያለ መደንፋት ጀመረባችሁ:: መደብ ከገመዱ ይጉተታልና ተመለሳችሁ ፍከይዝማችሁ ገባችሁ::

ምክንያቱም ደግሞ ሰሞኑን ባርያነት ያንገፈገፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ አፄን አኩሪና ታላቅ የትግል ምዕራፍ ከፈተ:: ለኛ ለተራማጆችም ብዙ እርጋታና ትጋ፡ሀ: ቀልጥፍናና የተጣራ አስተሳሰብ የሚጠይቅ ታሪካዊ አጀራ ትከሻችን ላይ ጣለብን:: መደብ ከገመዱ ይጉተታልና እናንተም እንደገና አንዳንዱ መናኛ "petty bpurgeois driven to frenzy " ርጋታ ሲያስፈልግ ድንፋታ፣ ትጋት ሲያስፈልግ ስንፍና፣ ግልጽ ፖለቲካ መስመር ሲያስፈልግ ውዥንብር የሚግርከው ሃንዉስ ከበርቴ ዝንባሌአችሁ አሸነፋችሁ::

ገና ንቅናቄው ሲጀመር ተቻኩላችሁ በ28/2/74 መግለጫችሁ ላይ "በኢትዮጵያ በኢምፔሪያሊስቶች ተነጠነሰሰ ኩዴታ ሊጣ ነው" ብላችሁ: ?ወንደም ነታችሁን አስጠነቀቃችሁን:: በዚህ "ተደናግጠን" ሳንጨርስና ገና ነፍስ ሳይዘራብን "የለም የቀደሙ በስህተት ነበር" እንኳን ሳትሉ "ቡሌቲናችሁ" ቁጥር 7 ላይ ደገመ በዚሁ በየካቲት ወር "የመጀመሪያው የኢትዮጵያ አብዩትም" ተደረገ አላችሁን:: ንዑስ ከበርቴው ከአንዱ ጫፍ ወደ አንዱ ጫፍ ለመቀያየር የተደነቀለት ፍጥነት እንዳለው ብናውቅም "የኛዎቹ" ባሳዩችሁ ፍጥነት አፄግ አድርገን ተደነቅን:: ግን ደግሞ በመሃል

"The partisans of the World wide Federation of Ethiopian students to their credit have anticpated the earthshaking events at home" 15 ብላችሁ የጻፋችሁትን ስናይ በእውነቱ ግብዝነታችሁ በጣም አሳፈረን:: ግን ደግሞ መላ ኢትዮጵያ በእናንተ ዙሪያ የምትሽከረከር ጉዳይ ነችና፣ ከናንተ ሌላ ተራማጅና አገር ወዳዱ የሚሉ ነነር ሃገራችን አልፈጠረባትምና፣ "የተጠነሰሰውን ሃፋሺስት ኩዴታ አክሽፈን ወደ መጀመሪያው የኢትዮጵያ ሬቮሉሽን የለወጥነው እኛ ነን" ብላችሁ መግለጫ አለማውጣታችሁን ለኢትዮጵያ ተራማጆች "ትሁትነት" እንደ አንዱ ዱለ ቆጥረነው ተደሰትን::

የሆነ ሆኖ የሰሞኑ የሕዝብ ትግል ይዘት እንኳን ተከትላችሁት ገብታችሁ ልታውቁትና ጊዜያዊ ተግባር ለትቀይሱ ይቅርና ነገሩ ሁሉ ስለምንም እንደሆነ የቷበጠላችሁ አትመስሉም:: ስለዚህም ባልገባችሁ ነገር እኛን ለማሳጣት ስትነሱ በሳቅ ገደላችሁን::

ግን ስለጊዜው ሁኔታ "ሳይንሳዊ ትንተናችሁ" ውስጥ ገብተን ከመዳከራችን በፊት አንዲት ነገር መዝግበን እንለፍ:: "<u>ድርጅቶች የሚሉት መሪ ቃል ጊዜው ያለፈበት ነው፣</u> ዘመኑ የሕዝባዊ ጦርነት ዘመን ነው: "እያለ ሳላገረሸባችሁ ፍከይዝም ዛሬ ስንት አጣዳፊ ነገር እያለብን አንከራከራችሁም:: አናደርገውም:: ጧም እንደሁ ይጠፋል፣ ሽለም እ ... ይገፋል፣ ተብሏል:: ያው ያስለመዳችሁን ድንፋታችሁ ከሆነ ግዱ የለም ይበርዱላችኋል:: ቋሚ ዕምነታችሁ ከሆነ /እንዲህ ዓይነት ነገር ታውቀ እንደሆ

*እናም አጣዳፊው ተግባር ፋታ ሲሰጠን እናንተም መንፈሳችሁ ተንሸ ሲረጋጋ እንከራከርበታለን:: ጊዜ ይሰጠን::

*በተከተሉት ወራት እንደታየው ይህ አድርባይ ቡድን ይቺን ተለካሻ አቋሙን ጨርሶ ከደመጣ የሚለውን የህዝባዊ ጦርነት ዘመን እንዳልነበረ ረስቶ "ምርጫ ይደረግ:: ጦርነት በመጣ ጠያቂው ደርጉ ነው:: እኛ የለንበትም:: ሰፊውን ህዝብ ማስታጠቅ በጭቆን በሄሮች ላይ ማዘመት ይሆናል" የሚል ሌላ "አቋም" /ያው ደግሞ ጨርሶ እስኪቀለበስ ድረስ/ ወስደ እናገኘዋለን:: "ሁለተኛው የወደኋላ ርምጃ" ተገላቻን ዜና 2ኛ ዓመት ቁ. 3 ህዳር 1967 ተመልከት እንደዚሁም "አድርባዮች ሲያጋልጡን..." ተገላቻን ዜና 2ኛ ዓመት ቁ. 4 መጋቢት 1967 ዓ.ም. ተመልከት::

ክፍል ሁለት: አንዳንድ ልዩነቶች ስለጊዜው ተግባራችን

መቸም ''የጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ'' ''የጊዜው አጣዳፊ ተግባር'' ሳይንሳዊ ትንተና'' የሚባል ነገር ስትሰሙ ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ነው:: ዛሬም እንደዚሁ ተጨንቃችኋል:: የት ነው ያለነው? ትግሉ በምን አግጣጫ ይቀጥል? ዛሬ በ1966 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ተራማጆች ምን እንሠራ? እነዚህ ሁሉ መልስ የሚጠይቁ አጣዳፊ ጥያቄዎች ናቸው:: ሁለታችንም ለንመልሳቸው ሞክረናል:: ስለዚህም በነዚህ ጉዳዮች ላይ የኛን ቀላልና ግልጽ አስተሳሰብ ለአንባቢ አስቀድመን እንገልጽለታለን:: እንዲያውም ካሁኑ ወዲያ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ሃሳባችንን ለመግለጽ የምንሞክረው በዚህ መልክ ነው:: መጀመሪያ አንባቢ ''ሳይደክምብን'' የኛን መሠረታዊ አስተሳሰብ እናሰፍርለታለን:: ከዚያ በኋላ በነገሩ የኛ ''ማርክሲስቶች'' ምን እንደሚሉ ለማስረዳት ከማጥ ውስጥ ጉትተን እናስገባዋለን::

እንግዲህ ከሀሁ ከጀመርን ልክ እንደእናንተው "Revolution is a process" እንላለን:: ከዚያም በሁለት ዋና ዋና ወቅቶች ይከፈላል ብላችሁ በመጀመሪያ ''ስፖንቴንየስ ፔርየድ'' አለ ትላላችሁ:: ከዚያም ይህ ወቅት ያልተደራጀና የአጭር ጊዜ ታክቲክም ሆነ የረዥም ጊዜ ዓላማ የሌለው ወዘተ ብላችሁ ስትነግሩን እኛም እንዲሁ "Spontaneously" ማንም ሳይነግረን ሌላው ወቅት ደግሞ የተደራጀ የትግል ዘመን ነው እንላለን:: ይህ ዘመን ደግሞ ልዩ መልኩ ተደራጅቶ የትግል ዘዴውን በታክቲክና በስትራቴጂ የሚካሄድ በዓላማው ደግሞ የመንግሥት ስልጣን ለመጨበጥ የሚደረግ ትግል ነው እንላለን::

ከዚህ ስልፈን ተርፈን ደግሞ አንድ ትግል የግድ ከሁለቱ ወቅቶች ማለፍ ስላለበት ''ካልተደራጀው የትግል ዘመን'' ወደ ተደራጀው የትግል ዘመን ለማለፍ ትግሉ መደራጀት አለበት ብንል አንባቢ እንደማይስቀብን ተስፋ አለን:: ግን እንበለው:: የተጣራ ነገር ጥሩ ነው:: ስለዚህም ዛሬ በኢትዮጵያ ወደሁለተኛው ወቅት መግባታችን ስለሆነ ወደሱም እንድንገባ፣ የድርጅቶች ጉዳይ ዋና ጊዜያዊ ጉዳይ ነው ብለን በጣም ቀላሉን ዕውነት አስፍረን እንለፍ::

የትግሉን ታክቲክም ሆነ ስትራቴጂ በሚመለከተው ጉዳይ መጀመሪያ አኛችን የሚወዱቀውን መጽሐፍ ብናገላብጥ /ለምሳሌ የስታሊን ፕሪንሲፕልስ ኦፍ ሌኒኒዝም/ ''የስትራቴጂ ዓላማው ጠቅላላውን ጦርነት ለማሸነፍ ሲሆን .... ታክቲክ ደግሞ ጠቅላላዉን ጦርነት ሳይሆን አንዷን ግጥሚያ ለማሸነፍ የሚወሰዱ ጊዜያዊና ተጨባጭ እርምጃዎችን የሚይዝ ነው.... ታክቲክ የስትራቴጂ አካል ሲሆን ለሱ ታዛዥና ለሱ አገልጋዮች መዋል አለበት:: 16 ይላል:: ስለዚህ ተራማጆች ድል ለማድረግ ከፈለጉ በደፈናው ''ጠቅላላውን ጦርነት'' ለማሸነፍ ስትራቴጂ ብቻ ማውጣት አይበ

ያቸውም:: በየዕለቱ ስለሚደረገው ትግልና ለሚለዋወጠው ሁኔታ "ታክቲካቸውን" መቀየስ አለባቸው:: ዛሬ ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጠረው ሁኔታ "ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም ይውደሙ ስለዚህም "ህዝባዊ ጦር ለዘላለም ይኑር" እያሉ ስትራቴጂን ቀይሶ ማወጁ ብቻ ከሆነ ከዛሬው ከዕለቱ ሃላፊነት መሸሽ ነው:: እንዲያውም ስለታክቲክ ዋናነት ሌኒን ሲጽፍ "....without this aspect materialism is incomplete, one sided and lifeless"

ይህ ሁሉ እንግዲህ ቀላል ቀላሉ ነው:: የኢዘናና የፌዴሬሽኑ "ማርክሲስት ማርክሲስቶች" ደግሞ እንደሚከተለው ነው:: ከላይ ያለነውን ሀሁ የፌዴሬሽኑ ቡለቲን "በቀላሉ" ሊያስረዳን ገጽ 6 ላይ እንዲህ ይላል:

"Since the revolution is a process it has its beginning and end. In this context, the whole course of the revolution may be observed on two big stages, the spontaneous period and the strategic period (?) The spontaneous period is that period of resistence by the peoplehaving no programmes of action and achieving political power, strategy tactics and organization characterized by rebellions; uprisings strikes and so on .....on the country, the strategic period ( ደገሙት!) is the period when the people start to struggle under programmes of action, political power, strategy, tactics and organization characterized by the existence of a revolutionary organization!" 18

ምን ፍኮይዝም ፍኮይዝም ትላላችሁ:: ሰውን ለማደናገር እንዲህ ያለ የተለየ ስጦታ እያላችሁ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን እንዲህ አድፍጠራችሁ ብትጥሉልን ትጸድቁ አልነበረም? "ስትራቴጂክ ፔርየድ" የምትሉትን ጉድ "የተደራጀ ዘመን" ብለን "እንምከርላችሁ" ብለን አስበን ነበር: ግን ደግሞ ዝቀ ብላችሁ በኢትዮጵያ "የድርጅቶች ዘመን አለፈ" era of organisations "ማለት" Right Opportunism" ነው "out moded slogan" ነው አላችሁን ስለዚህም የኛ "ማርክሲስቶች" ጥበብ ካምስጢረ ሥላሴ የረቀቀ ጉዳይ ይሆንብናል:: ስለዚህ ገና ብዙ የተደገሰለት አንባቢ ስለተደራጀና ያልተደራጀ ትግል እንዲሁም ስለታክቲክና ስትራቴጂ የኛን ቀላል ቀላሉን ይዞ "የማርክሲስቶቻችንን" "የዓረፍተ ነገር ክምር" አይቶ እንዳላይ እንዲፍለፈው እንጠይቀዋለን:: የት ነዉ ያለነው?

ቀላሉ አነጋገር ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ "ስፖንቴንየስ አንሰርጅ" ወይም ያልተደራጀ ትግል ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል:: የህዝቡ የትግል ደረጃ ከዚያ ይበልጥ ከፍ እንዲልና ድልን እንዲጎናጸፍ የግድ መደራጀት አለበት የሚል ነው:: ስለዚህ ተራማጆች ፊውዳሊዝምንና ኢምፔርያሊዝምን የሚታገሉትን ኃይሎች በሙሉ በፈርጁ በፈርጃቸው እንዲደራጁ ማገዝ እነዚህም ኃይሎች በአንድ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ስር እንዲተሳሰሩ ለማድረግ መታገል አለባቸው::

እነዚህ ጊደኞች እኛን ያሳጡ መስሏቸው "They say the objective conditions are ripe but the subjective conditions are not" ይላሉ:: <u>አወን እንዲህ ብለናል: አሁንም እንላለን</u>:: ግን ደግሞ ተራማጆች የህዝቡ የፖለቲካ ንቃት ደረጃ አልተሟላም ሲሉ ህዝቡ በሪቮልሽኑን ከግሉ አድርሶ ሥልጣን ለመጨበጥ አስፈላጊው ድርጅትና ንቃት የለውም

ስለዚህ ይበልጥ እናንቃው ይበልጥ እናደራጀው በማለት ነው:: እኛም ዛሬ "አልተሟላም" ስንል ከፍ ያለ የፖለቲካ ቅስቀሳ የማደራጀት ጥረት ያስፈልጋል ለማለት ነው:: ግን ዝቅ ብለን እንደምናየው እናንተ ይህንን የንቃት ደረጃ እንዲህ ለማጋነን የምትሞክሩት ይህንን ይፖለቲካ ቅስቀሳና የማደራጀት ተግባር ለማናናቅ እየፈለጋችሁ ነው::

እንደዚህም ስለሆነ በ"ሰብጀክቲቭ ኮንዲሽንስ" ጉዳይ ያላችሁ አስተሳሰብ ከመጠን በላይ ሰብጀክቲቭ ነው:: እናንተ በግራ ጎናችሁ የተነሳችሁ ለት ነገሩ ሁሉ "ቀፍናል" ትሉና ስለሀገሪቱ ሁኔታ ስትጠየቁ:_

"The objective conditions or prerequisite for revolution are ripe whilethe subjective conditions have not yet fully matured." 19

ትሉናላችሁ በቀኝ ጎናችሁ የተነሳችሁ ለት ደግሞ ነገሩ ሁሉ ከጸሃይ ደርቶ ይታያችሁና "ዛሬ ጊዜው እንዴት ነው" የተባላችሁ ይመስል "ተሟልቷል" ስትሉ

"The present situation in Ethiopia is characterized by the existance of a revolutionary situation without the existance of a revolutionary party."10

ትሉናላችሁ::

እንደዚሁም ደግሞ እናንተ"ብዥ" ብሉባችሁ የተነሳችሁ ለት "ሰብጀክቲቭ ኮንዲሽንስ" ነገር እንዲህ በቀላሉ የሚደረስበት ምስጢር አይደለም እያላችሁ ስትደናገሩ

"To be sure, the energence of the subjective forces will be regualated by the class relations of state apparatus and external and internal alliance of the forces of retrogression in as much as the power of the people"21

ትሉናላችሁ ግን ምን ማለታችሁ ይሆን?

"To be sure" እናንተ "ማርክሲስቶች" ነገሩ ሁሉ ፈጽሞ ምስጢር የሆነባችሁ ይመስላል:: ግን ይኸ ሁሉ ማደናገሪያ ዘራችሁ ዘራችሁ የሕዝቡን የንቃት ደረጃ ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል ብላችሁ የማደራጀቱን ነገር ለመናቅ ነው:: ግን አይሠራም:: ህዝቡ ሳይቀሰቀስና ሳይደራጅ ሺህ ጊዜ ነቅቷል ብትሉን፤ እና ደግሞ በዚህ ላይ ቢደራጅና ቢቀሰቀስ ሚልዮን ጊዜ ይነቃል እንላችኋለን:: ስለዚህም ምንጊዜም ቢሆን ከና ይበልጥ የቅስቀሳና የማደራጀት ተግባር ይጠበቅብናል ማለት ነው:: ሌኒን እንዳለው

"We have become convinced that the fundamental error commitied by the 'new trend' in Russian social democracy is its bowing to apontaneity and its failure to understand that the apontancity of the masses demands a high degree of consciousness fro m us social democrats. The greater the spontaneous upsurge of the masses and the more widespread the movement, the more rapid, incomparably so, the demand for greater consciousness in the theoretical, political and organisational work of social democracy." 22

የኢትዮጵያ ማርክሲስቶች ግን ያለቅስቀሳና ያለድርጅት በቅስቀሳና በድርጅት የሚደርስበት ደረጃ ደርሰናል ነው የሚሉን:: ከዚህ አስከትለው ስለማደራጀት ጉዳይና ስለቅስቀሳ ጉዳይ ሲጠየቁ "የምን ድርጅት፣ የምን ቅስቀሳ፣?" ብለው ቀጥታውን ነገሩን ሁሉ ቢዘጉትና ዝም ቢሉ በዚህ ዋና ጉዳይ ላይ ሰውን ስለሳደናገሩብን ብቻ ለኢትዮጵያ ሪቮሉሽን ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳረጉ ቆጥረንላቸው እንገለገል ነበር:: ግን እነሱ በየት?:

## ድርጅቶች የሚሉት "ዘመን ያለፈበት"ፈሊጥ? ?

እንደለማዳችን "ማርክሲስቶቹ" አንባቢን ሳያደናግሩብን የኛን አስተሳሰብ እንናገር:: ዛሬ የኢትዮጵያን ህዝብ ትግልና የፖለቲካ ንቃት መቸም ያልተደረሰበት ከፍተኛ ደረጃ ላይ

ደርሷል:: በህዝቡ ትግል የኢትዮጵያ ጠላቶች ተደምስሰው ህዝቡ ስልጣን እንዲጨብጥ ዛሬ በሃገራችን ያሉ ጸረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በሙሉ በፈርጁ በፈርጃቸው መደራጀት አለባቸው:: በዚህ መልክ የሚቋቋሙት ፖርቲያችና ልዩ ልዩ ሰፊ ህዝባዊ ድርጅቶች በአንድ የጋራ ፕሮግራም ላይ ተቻቻብረው እንዲታገሉ አንድ ዲሞክራቲክ ግንባር ማቋቋም አለባቸው:: ይህ ዲሞክራቲክ ግንባር ድልን ተጎናጽፎ ህዝባዊት ኢትዮጵያ የምትመሠረተው አመራሩ በሠራተኛው ፖርቲ እጅ ሲገባ ብቻ ነው:: ስለዚህ የተራማጆቹ ተግባር እነዚህ ፖርቲያች እንዲቋቋሙ፣ የሃሳብ የንግግር፣ የመጻፍ፣ የመደራጀትን የመሰሉት መብቶች በሃገራችን እንዲረጋገጡ መታገል ነው:: በውነቱ ይኸ ሁሉ በጣም ግልጽ ይመስለናል::

አንባቢ ብርታቱን እንዲሰጠው እየጸለይንለት እንግዲህ ወደ "ማርክሲስቶቹ" ሐስተሳሰብ እናስገባው:: በዚህ በኩል ያላቸውን አስተሳሰብ ብናጠቃልልላቸው "የድርጅቶች ዘመን" ማለት ጊዜው ያለፈበት መፈክር/አውትሞድድ ስሎጋን/ ስለሆነ "ቢበዛ" አንድ የሠራተኛ ፖርቲ እንዲቋቋም መታገል ነው ይሉናል:: ነገሩን መልክ እየሰጠነው እንሂድ:: መጀመሪያ "የድርጅቶች ዘመን" እንዴት ጊዜው እንዳለፈበት እንጠይቃቸው:: ከዚያ በኋላ ዛሬ ዲሞክራሲ እንዲስፋፋ የምንታገል ሰዎች በምን ፊሊጥ አንድ ፖርቲ ብቻ እንዲቋቋም መታገል እንዳለብን ምስጢሩን ከቻሉ ይገልጹልናል:: ከዚያ ደግሞ ገና የሚፈጠረው ፖርቲ ገና የሚታሰበውን ግንባር ከመጀመሪያው ካልመራው እያሉ እንዴት ጡብ ያለሽ በዳቦ እንደሚያያይዙን እንመለከታለን::

የድርጅቶች ጉዳይ እንዴት ዘመኑ እንዳለፈበት "ሲያስረዱን" የጀምሩት ያለድርጅት ን የሕዝብ ንቃት ደረጃ በድርጅት የሚደርስበት ደረጃ ደርሷል በሚለው አዲሱ ቲዎሪያቸው ነው::

"በአንድ የፖለቲካ ድርጅት የረዥም ጊዜ የፖለቲካ ቅስቀሳ በኋላ ገበሬዎች ተገንዝበው የወደፊቱን ሳይፈሩ ቆርጠው ለመታገል እንዲበቁ የሚያደርገውን የተለመደ የሬቮሉሽን እርምጃ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ያለአንዳች የፖለቲካ ድርጅትና ቅስቀሳ ...ጀምረውታል"

መጀመሪያ ነገር እናንተም "የወደፊቱን ባትፈሩ በታላቶቹ በማርክስና በሌኒን ስም እንዲህ ጥልቀት ያለው አነጋገር ደፍራችሁ በመጻፋችሁ ለፂቲዮጵያ "ማርክሲስቶች" ደፋርነትና ጀግንነትንም አንድ ቋሚ መረጃ ትታችሁ ማለፋችሁን ተረዱለን::

በተረፈ ግን በዝብርቅርቅ ሃሳብ ያሰለቸን ሰዉ መጥቶ "ያለስኳር የጠጣሁት ሻይ ስኳር ስኳር አለኝ" ቢለን አጉል ንትርክ ያደክመንና በተለይ ደግሞ ሌላ አጣዳፊ ተግባር ያለብን ሰዎች ከሆንን በፈገግታ "ጮ.ቸስ የእግዜር ተዐምር ምን ማለቂያ አለው? ለሱ ምን ይቸግረዋል" ብለን መገላገል እንችላለን:: ነገር ግን ከዚህ ተነስቶ "ስኳር የሌለው ሻይ ስኳር ስኳር ይላልና ከዛሬ ጀምሮ እናንተም እንደኔ እንድትጠጡ ይሁን" ብሎ ሊበይንብን ቢነሳ የተዐምሩን ቀልድ ርግፍ አርገን ትተን ሰውዬ "ሰብጀክቲብ" አስተሳሰቡ አሸንፎት ነው እንጂ ስኳር የሌለው ሻይ ስኳር ስኳር ሊል እንደማይችል "ለማስረዳት" ወገባችንን ይዘን እንነሳለን::

ያለድርጅትና ያለቅስቀሳ የአንድ ህዝብ የፖለቲካ ህሊና በድርጅትና በረዥም ጊዜ ቅስቀሳ የሚደርስበት ደረጃ ደረሰ የሚለውን በሬ ወለደ እንዲሁ በፈገግታ ብናሳልፈው በውነቱ ግድ የለንም ነበር:: ነገር ግን ሰውዬው በዚህ "ስፖንቴንየስ አፕሰርጅ" ተማርኮ የቅስቀሳውን ተግባርና የማደራጀቱን ሃላፊነት በመናቅ ጊዜው የጠር ዘመን ነውSEIZE THE TIME! SEIZE THE GUN! እያለ ሲደነፋብን ግን ሌላ ጉዳይ ነው:: እነዚህ "ጌደች" የሚያመሩት ወደዚያው ነው:: ስለዚህም አንድ ጌድ እንዳለው የሚከተለውን የአረፍተነገሮች "ክምር" ስናነብ በጠቀሳሳዉ ለኢትዮጵያ ተራማጆች በተለይ ደግሞ ለነዚያ ለመከረኛች ለማርክስና ለሌኒን ሃፍረቱና ሃዘን ተሰማን::

"All these attest that the people are more than ever conscious and determined to struggle for the conquest of political power. Hence the period can only be characterized as the era of the protracted peoples's war and not the era of the 'necessity of organizations since era refers to a specific historical stage a society is passing through and the time of the necessity for a party is quite another thing? "The right opportunist alternative ot the general characteristic of present day Ethiopia <u>is the empty talk and outmoded slogan era of the necessity of organizations</u>." 24

እዩ "ጓዶች"፡ ሺህ ጊዜ እነጋገር ብታሳምሩ፣ ሺህ ጊዜ ሠራተኛው መደብ "ሪቮሉሽን" "የሠራተኛ ምራሊቷ" እያላችሁ በቃላት ስትጫወቱ ብትውሉ ቀልዩ ብሎ ከሚታየው ተግባራችን በሆነ ባልሆነው ተለካሻ ቱወሪ ተሸፋፍችሁ ልታመልጡ አትችሉም።

አሁንማ <u>በየካቲት 1966 ዓ.ም.</u> የኢትዮጵያ ተራማጆች <u>አጣዳፊና ጊዜያዊ</u> ተግባር ምን ድን ነው ብላችሁ ስትጠየቁ ጨርሶ በገባችሁበት፡

በኋላ ከገባችሁበትማ አሁን ያለንበት ዓለም የቡርዡዋ ሪቮሉሽን ኤራ አልፈን ሶሻሊስት ሪቮሉሽን ኤራ ገብተናል።እናንተም በትክክል ስትጽፋ ኤራ ማለት"a specific surande historical stage asociety is passing through" ትሉታላችሁ። ሌኒን ደግሞ ነገሩ ከመርዘሙ የተነሳ "The yard stick of world history " ይለዋል። እንደዚህም በጣም ረዥም ጊዜን ስለ ሚያመለክት <u>ዛሬ</u> የሃገራችን ሁኔታ ምን ተግባር ይጥለብናል ለሚለው ቀልጭ ያለ ጥያቄ ያለንበትን "ኤራ" ለይቶ ማወቁ እምብዛም የሚረዳን ነገር የለውም። ይኸ "ኢምፔሪያሊዝም በኢትዮጵያ የሚያሳየው መልኩ ምንድን ነው? እንዴትስ አድርገን እንዋጋው?" ብላችሁ ስትጠየቁ "ኢምፔሪያሊዝም መጥፎ ነው። እንደምንም ታግሎ መጣል ያስፈልጋል" ብላችሁ እንደመመለስ ያህል ነው። ስለ ኤራ ማውራት ምንም ክፋት የሌለው ነገር ሆኖ ሳለ በቱጨባጭ መንገድ የጊዜን ተግባርና ታክቲክ ለመቀየስ ሲሆን ሳንቲም እንደማይረዳን ለማስረዳት ሌኒን ኤራ የዓለም ታሪክ ዘመን መሳኪያ ሜትር ነው ካለ በኋላ

"But world history is counted in decades. Ten or twenty years earlier or later makes no difference when measured with the yardstick of world history; from the standpoint of world history it is a triffle that cannot be considered even apporoximately. <u>But for that very reason, it is a glaring theoretical error to apply the yardstick of world history to practical politics!</u>" ፳፭

ብሎ ያስጠነቀቃችኋል።

ለዚያውም እንግዲህ የምትኖሩበትን ዘመን ካወቃችሁትና ኤራን ያህል ትልቅ ነገር ካልተሳሳታችሁ ነው። ወይም ደግሞ "we beliveve there is a big difference between [illegible]1972 Ethiopia and 1974 Ethiopa" እያላችሁ በሁለት በየሶስት ዓመቱ ከኤራ ኤራ የዘለላችሁ እየመሰላችሁ ካልተንቀራጠጣችሁ ነው። እናንተ ግን ዘመን መሳሳታችሁ አለበቃ ብሎ አንድ ኤራ እንዲህ ባጭር ጊዜ አለፈ ልትሉን ይቃጣችኋል። ነገር ግን እንኳን ሁለት ሶስት ዓመት ይቅርና ኤራን ያህል ነገር ቀንሳችሁ ቀንሳችሁ "ከመቀጸበት" በአንዱ አገር ሰማይ ላይ ብዥ ብሎ የሚያልፍ ነገር ብታደርጊት እንዲህ "ነዶርዴቶች ኤራ" በኢትዮጵያ ሰማይ ላይ ገና ሲያልፍ አለመታየቱን እናረጋግጥላችኋለን።

ግን እነጋገራችሁ ምናልባት ልክ ከሆነ በጣም ወደኋላ /ቢያንስ አንድ አራ/ ቀርተናል ማለት እኮ ነው፡ እንዲህ ሆኖ ነው እንጂ እንዴት በየመጽሄቶቻችን ላይ ይህንን "አውትሞዱድ ስሎጋን" እኛን ብለን ይዘን "ንነዘንዝ ነበር? በትግላችን ቁ. 4 ላይስ ገና ሽፋኑ ላይ "ጊዜው የፖለቲካ ፓርቲያችን መመስረት ይጠይቃል" ብለን እንዴት እንጽፍ ነበር? እንዲህ መሆኑን ቀድሞ አርጋችሁ ሳትነግሩን ነዉ እንጂ የመንግሥቱ ጀሌ ቀላጤያች በጋዜጦች ላይ እንደናንተው ፓርቲያች አያስፈልጉም እያሉ "ፓርቲያችን ለማቋቋም ያለው ፍላጉት የሚመነጨው የሃገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ጨርሰው ከማያውቁ ሰዎች ዘንድ ነው፡፡" እያሉ ህዝቡን ሲያወናብዱት "አወን ዕውነታችሁን ነው፡ "ማርክሲስቶች" ጊዜው ያለፈበት ነው ብለዋል" እንላቸው አልነበረም? ደግሞስ በዚሁ መጽሄታችን ላይ ዘመኑ እንዳለፈበት አንደኛ ገና ሳይሰሙ "ፓርቲያች፡ ፓርቲያች፡" እያሉ የሚጮሁትን "ተማሪያች፣ ምሁራን፣ ላብአደር፣ ወታደሮች... እንደገፋለኝ" ከማለት ይልቅ የናንተ "መምሪያ" ሳይደርሰን ነው እንጂ "ቱው ዝም በሉ "ማርክሲስቶች" እንዳይሰሟችሁ" እንላቸው አልነበረም?፡ የናንተ "መምሪያ" ሳይደርሰን በዚሁ ጉደኛ "ትግላችን" ላይ ፣ዚህን የፓርቲያች ጉዳይ የጊዜው ዋና ጉዳይ አድርገን ገጽ 36 ላይ "በዛሬው ወቀት በኢትዮጵያ ሕዝብና በገዥው መደብ መጠከል ያለው ትግል በዚህ በፓርቲያች መቋቋምና አለመቋቋም ጉዳዩ ሆንዋል ብንል ተሳሳትን አይመስለንም" ብለን ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ አዲሱ ርቮሉሽናዊ አስተሳሰብ" ከደረሰን ወዲህ በሚቀጥለው መግለጫው ላይ ማህበራችን "በዛሬው ወቀት በኢትዮጵያ ህዝብና በኢትዮጵያ "ማርክሲስቶች መካከል ያለው ትግል በዚህ በፓርቲያች መቋቋምና አለመቋቋም ጉዳይ ላይ ነው" ብሎ እንዲጽፍ እንጠይቃለን፡፡

አይ "ጓዶች" ግን ደግሞ ይህን "ዘመኑ አለፈበት" የምትሉትን ፈሊጥ ይዘን "የለም ዛሬ የፖለቲካ ፓርቲያች ለኢትዮጵያ ህዝብ "እንደ ህይወት እስትንፋስ" ያስፈልጉታል ወዘተ እያልን ዕምነታችን ይኸ ነው የምንሠራውም በዚህ አቀጣጫ ነው እያልን ወገባችንን ይዘን ብንከራከራችሁ ምንኛ ደስ ባለን ነበር፡

ግን እናንተ በየት በኩል፡ በንቁና ቄያችን ውስጥ ውዥንብር ለመንዛት እንጂ በምንም የፖለቲካ ጉዳይ ላይ ቆሞ ለመከራከር የፖለቲካ አቋማችሁን የንውስ ከበርቴ ቅንጥንጥነት ያጠቃዋል፡፡ውል ለያዘ ክርክር ፍላጐቱም፣ ችሎታውም ትዕግሥቱም የላችሁም፡፡ ስለዚህም በማህበራችን ላይ የምታቀርቡትን "ክስ" በዓይነት በዓይነቱ ተከፋፍላችሁታል፡፡ ፈደረሽናችሁ ፓርቲያች ካልተቋቋሙ እያልን በታገልን "የቀኝ አድርባይ" እያለ የሚለቀውን ውርጅብኝ ገና አዋህደን ሳንጨርስ የሱን ክስ ጨርሶ የሚያጣፋ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ማህበራችን የሚፈጽመው ሌላ "ወንጀል" ይዛችሁለት ብቅ ትላላችሁ፡፡ በዚሁ "ሰምቱዉትስ" ገጽ 32 ላይ ደግሞ "እንደራጅ እናደራጅ" እሉ ስትሉ እንዲህ ትላላችሁ

"When the people that want revolution ädvance the iedea that it is time thatthe subjective forces be organized, the camp of the desperades, opportunists and intellectual tourists of our country decry this correct and scientific stand. They heap abuses overabuses and subterfuges oversubterfuges calling all and sundry 'ultraleft' 'treasons. 21

በደረጣ ጦርነት መልክ ከየአቀጣጫው ማዋከብ /በናንተ የንውስ ከበርቴ ደንፋታ የሚደናገጥ ያለ ይመስል፡/ ሥራዬ ብላችሁ ይዛችሁታል፡፡ ስለዚህ በዚህ መልክ ደግመ "ለድርጅት እንቅፋትነታችን" የተከሰስንበት ጽሁፍ ገና ቀለሙ ሳይደርቅ "ፈደረሽናችሁ" /የዱርዬዎቹ ዘመን አልፏልና የድርጅት አባል መሆን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እንደተፈጸመ ወንጀል ይቆጥረዋል

መስል፡፡/ በ5/5/74 ባወጣው መግለጫ ላይ መሠረት በሌለው ልብ ወለድ አነጋገር "የአውሮጳ መሪያቸና መሪያቸ የነበሩ ሰያቸ የሚኢትዮጵያ ብሄራዊ ነፃ አውጭ ግንባር የተባለዉ ድርጅትአባሎች መሆናቸውን "አያረጋገጠ" ለፖሊስ ፡ያስረከባቸዋል።

ይህን ጊዜ ፈጽሞ ግራ ይገባናል፡ የለም አይደለም፡፡ ይህን ጊዜ ነገሩ ሁሉ ግልጽ ይሆናልናል አንደኛ ከናንተ ጋር በምንም ዓይነት ቁም ነገር ላይ ውል ያለው ክርክር እንደማ ይቻል ግልጽ ይሆናል፡፡ ሁለተኛ አንሃይለሥላሴ በጥይትና በፋሽስታዊ ግፍ ያሳበረዱትን ስመጥ ሩውን የኢትዮጵያ ተማሪያቸ ንቅናቄ <u>ከውስጡ ሆናችሁ በማወናበድና በመስነጣጠቅ ብቻ ለመበተን</u> እንደተነሳቸሁ እኛ ቀደም ብለን የደረስንበትን ግምት ቁ፻ንለማጣራጩ‐ሁሉ ያየዋል ፡፡ ነገር ግ ን ይህንን ርኩስና አድሃሪ ሙከራችሁን የኢትዮጵያ ተራማጆችና አገር ወዳዶች ተረዳድተው በማ ከሸፍ ላይ ናቸው ፡፡

ስለዚህ አሁንም ፡"ስለመሳመራቸሁ" እንቀጥል በድርጅት ጉዳ‌ዩ "'አለን የምትሉት ሌላው አቋም /ደግሞ 'አልወጣንም ባለመግባባት ነው ስንደ እና ሌላ ነው ያሽነው' እስከትሉ ድረስ/ የተማረው ንቅናቄ"ፓርቲያቸ" "ድርጅቶቸ" የሚለውን ጊዜ ያለፈበትና የቀኝ አድቭ ዮችአቋም ተቶ የሠራተኛ ፓርቲ ብቻ እንዲቋቋም የታገለ የሚል አቋም ነው ፡፡ እዚሁ "ሳም ቶውትስ.." ውስጥ በየጋዱ ያዘ ለቀቀ እያረጋቸሁ ትጠቀሱልናቸላቸሁ ፡፡ ነገር ግን ነገር ለመዘባረቅ ሲሆን የማ ያዳግምናአህል ውሃ የማያስገ "ግልጽ አነጋገር ያለው "ፊደሬሽኑ" እንዲህ ይደነግጋል ፡፡

"Moreover ESUE and ESUNA, as far back as 1972 had resolved to agitate for the creation of the PARTY OF THE PROLETARIAT and NOT for 'many organizations'." 16

ግሩም ነው፥ ግን "የሠራተኛ ፓርቲ" የሠራተኛ ፓርቲ ብቻ" በሚል ሽፋን የንዑስ ከበርቴ ድንፋታቸሁንና የሠራተኛው መደብ ትግል ዕንቅፋትነታቸሁን ለመሸፈን በፍጹም እንደማትቸሉ እናሳያቸሁ፡

መቸም አንድ ሰው "ማርክሲስት" ነኝ ስላለ ብቻ "አለበሳም መልኬ በቃኝ" እንደሚባው "ኦሳስበም'ማርክሲስትነቱ ይበቃናል"ሊል አይቸ'ም፣ እንደዚህም ስለሆነ "ማርክሲስትነታቸንም" ሁለት በጣም ቀላ' የሆኑ ነገሮቸ እንዲያስቡ እንጠይቃቸዋለን ፡፡

አንደኛ መጭው ሪቮሉሽን ሶሻሊስት ሳይሆን አዲስ ዴሞክራቲክ ነው፡ ብለናል ፡፡ ብላቸ ኋ' ፡፡ ይህ ሪቮሉሽን ደግሞበሠራተኛው መደብ ብቻ ሳይሆን በሃገሪቱ ባሉት ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት የጋራ ትግል የሚፈጠ ነገር ስለሆነ እነዚህ ሃይሎች አንድ የጋራ የሆነ ሪቮሉሽናዊ ግንባር መፍጠር አለባቸው ብለናል ፡፡ ብላቸኋል ፡፡ ትግሉ ከግቡ እንዲደርስ ግንባሩን በሠራተኛው ፓርቲ እንዲመራ ያስፈልጋል ፡፡ ብለናል ፡፡ ብላቸኋል ፡፡ ከዚህ ተነስተን ይህ ህዝባዊ ግንባር ኃይል የሚኖረውና ሠራተኛውም ድኑ አጋዥ የሚያገኘው ተቀጊያቸ ሁሉ በፈርጅ በፈርጃቸው ተደራጅተውና ጠንክረው ሲተጋገዙ ነው እንላለን ፡፡ ይህ ለማንም ግልጽ የሆነ "ምስጢር" ለእናንተ እንዴት አልታያቸሁ አለ፥ "መሪው" ብቻውን ተደራጅቶ ሌሎች ተቀጊያቸ ካልተደራጁና "መሪው" ብቻውን ከጠላት ከተጋፈጠ ጠቀሳሳው ትግል እንደሚዳከም እንዲገባቸሁ ለየትኛው ታቦት እንሳልላቸሁ?

እናንተ "ከ'ናት ትሻል ሞጊዚት" ሰንዳሉ የሠራተኛ ፓርቲ ብቻ "እንቋቁምለት" "ትሉለታላቸሁ" እንጂ የኢትዮጵያ ሠራተኛ መደብና <u>ዕውነተኛ ማርክሲስቶቸ ዛሬ በኢትዮጵ</u>ያ ፀረፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎቸ በሙሉ "ታውቀ በሚደድቀላቸው "ዓላማቸው ላይ ተደራጅተው እንዲተጋገዙ ይጥራሉ ፡፡ ስለዚህም እንዲደራጁ መቀስቀስና ማገዝ የሁሉም ተራማጅ ተግባር ነው ፡፡ ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው ይባላል ፡፡ ስለዚህም እናንተ በድንፋታ፣ በወሬና "ስሳይንሳዊ ትንተና"ብቻ "ለምትሳተፉበት" ትግል አጋዥ የመሰብሰቡን ጉዳይ ቸላ ብትሉት ፈጽሞ

አይደንቀንም ። በርግጥ የሚታገሉ ተራማጆች ግን የህዝቡ ወገን የሆነ ሁሉ እንዲደራጅና እን ዲጠናከር የማይቀጠብ ጥረት ያደርጋሉ ።

ሁለተኛ ደግሞ ራሱ የሠራተኛው መደብ የፖለቲካ ህሊናውን ከፍ እንዲያደርገውና የጠነከረ ቋሚ ፓርቲ እንዲቋቋም ከተፈለገ እንኳን እኛ "ሰፊው ንቅናቄ" ይቅርና እናንተም "ማርክሲስቶች" ብትሆኑ ተቀዳሚ ግዴታችሁ /ግንባር ቀደሞች ናችሁና/ በየመደቡ እየገባችሁ ማንቃት ማስተማርና ማደራጀት መሆኑን እንዴት ትስተታላችሁ? እናንተ የራሳቸሁትን ሌኒን ሊያስታውሳችሁ እንዲ ይላል ፦

"To bfing political knowledge to the WORKERS the social donocrate must GO AMONG ALL CLASSES OF THE POPULATION. THEY must dispatch unite of their army in ALL DIRECTIONS."

እንዲህም ካለ በኋላ ነገሩን "ኢኮኖሚዝም" ለማድረግ በትልቁ "ለሠራተኛው ፓርቲ ብቻ" እያላችሁ የተገለ አቀድ የምታስናዱትን "ማርክሲስቶች" ለመመለስ በቋነዘረ አነጋገር እንደገና እንዲህ ይላል ።

"We must go among all classes of the population. as theoriticians., as propagundists, as agitators and as organizers;"

እንግዲህ የናንተ "የማርክሲስቶች ተግባር እንዲህ ከሆነ የሰፊው ተማሪ ንቅናቄ የቀስቀሳና የማደራጀት ጥረት በምን ፈሊጥ እንደዚህ ሊጠብ እንደሚችል ፈጽሞ አይገባንም ። ይህ እንዴት ይቻላል? አቅሙስ አለ ወይ? በሌሎቹ መደቦች ውስጥ ለእንዲህ አይነት ሥራ አመቺ አካባቢ አለ ወይ? ደግሞስ ይህ ከሠራተኛው መደብ ፈቮሉቮናዊ አቋም ወደኋላ ማለት አይሆንም ወይ? ከዚቹው ጥቀስ አከታትሉ ሌኒን እነዚህን ሁሉ የዛሬ 70 ዓመት መልሶላቸኋልና አይቀቸው ።

እነዚህ "ጓዶች" ዛሬ የተማሪ ንቅናቄያችን የሠራተኛው ፓርቲ ብቻ እንዲቋቋም መታገል አለበት ሲሉ የሚሰጡንን "ምክንያቶች" ስናይ የአንድ ሰነፍ ህጻን ተማሪ ታሪክ ትዝ አለን ። ይህ ተማሪ ዓመም ክብ ለመሆኗ ሶስት ማስረጃ አምጣ ተብሎ ግቢ ነፍስ ውጭ ነፍስ ሆነበት ። በመጨረሻም መረጃዎች ሲደረድር 1ኛ/ አባቴ ብለዋል 2ኛ/ እማዬም ስትል ሰምታለሁ 3ኛ/ አስተማሪዬም ብለዋል ይባላል ብሎ ደመደመ ።

እነዚህም ጓዶች ይህን ያህል ትልቅ "ጥሪ" ፈልስ ፈው ሲያቀርቡ ይህ አቋማቸው በምን ተዕምር ከኛ አቋም እንደሚሻልና እንዲትስ የነፃነትን ትግል በተሻለ እንደሚያግዝ ሲያስረዱን ሶስት ምክንያቶች ይሰጣሉ ። 1ኛ/ As far back as 1972! በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር ለሠራተኛ ፓርቲ ብቻ እንድንታገል ወስኗል ። 2ኛ/ As far back as 1 972! ኢዙናም እንደዚሁ ወስኗል ። 3ኛ/ ከፈለጋችሁ ደግሞ "The agitation for the necessity of a Revolutionary party is never (!) a new thing!" [28]

እንግዲህ በእነዚህ ጥልቀት ባላቸው ምክንያቶች መማረክ "አቀቶት" "ፓርቲያች" "ፓርቲያች" ህዝባዊ ግንባር" ወዘተ እያለ ህዝቡን ሊያደናግር የሚያዘ ተማሪ፣ አገር ወዳድ ማርክሲስት፣ ወታደር፣ ወዝአደር ...ሁሉ ድርጅቱንም ለመከዳት አደብቶ የሚጠብቀ "የቀኝ አድርባይ" ነውና አንባቢ እንዲያጋልጠው አደራ እንላለን ። እንደዚሁም ደግሞ በግንባሩ አመራር ጉዳይ የማህበራችን ውሳኔ ሬቮልሽኑ "SHOULD be led by the proletariat" ማሆኑ እየታወቀ <u>ዛሬ</u> ትግሉን ሠራተኛው አይደለም የሚመራው፣ ወይም እስካሁን የተደረገውን ትግል

"In fact it is the petty bourgeois that has led the struggle to this day "

ብሎ ደፍሮ የሚናገር ሁሉ 'በቀኝ አድርባይነት' በዚሁ መልክ እንዲጋለጥ አደራ እንላለን ::

አሁን ደግሞ ወደ ሪቮሉሽኑ አመራር ጉዳዩ እንግባ :: እንዲያውም አንዱ "መሰሻቸን" ይዘው ነውና እሱንም ባጭሩ እንመልሰላቸው ::

"They have finally come out with their pettybourgeois lovestory which they have occasionally been insinuating since the Hanover Congress. They say "the Reovolution can be led by the petty bourgeoisie. In fact it is the petty bourgeoisie that has led the struggle to this day" where are these gentelmen moving their wheelchair, this time when they know very well that it is the position of the student movement that the revolution SHOULD be led by the proletariat." 28

ወደነሱ ትንተና ከመግባታችን በፊት የኛን አቋም እንግለጽ :: ሪቮሉሽኑ ከግቡ ሊደርስ የሚችለው የሠራተኛው ፓርቲ ግንባሩን ሲመራው ብቻ ነው :: የሠራተኛው ፓርቲ ይህን አመራር ሲይዝ የሚችለው "አመራሩ ይገባኛል" ብሎ የማህበሮቻችን ውሳኔ እየጠቀሰ አይደለም:: በግንባሩ ውስጥ መራራና የተወሳሰበ ትግል በማካሄድ የሚገኝ ግንባር ቀደምነት ነው :: የድርጅት ነፃነቱን፣ የፕሮፖጋንዳና የአጅቴሽን የማድረግ መብቱን፣ በግንባሩ ውስጥ ዲሞክራሲ መጠበቁን እስካረጋገጠ ድረስ የሠራተኛው ፓርቲ ግንባሩ የተቋቋመ የዕለቱ ለት የመራሩን ቁልፍ "ካልተረከብኩ አልታገልም" ሊል አይችልም :: የሠራተኛው ፓርቲ ሪቮሉሽኑን ከግቡ ያደርሰዋል ስላልን ከመጀመሪያው እሱ ይመራዋል ወይም መምራት አለበት ማለታችን አይደለም :: ንዑስ ከበርቴው ደግሞ ሪቮሉሽኑን ከግቡ አያደርሰውም ስላልን ትግሉ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ባለበት ጊዜ የግንባር ቀደምነቱን ቦታ ሊይዝ አይችልም ፡ ማለት አይደለም ::

እነዚህ ጓዶች ከመጀመሪያው ሁለት ነገሮች ያደበላልቃሉ :: መጀመሪያ "ሪቮልሽኑ በንዑስ ከበርቴው ሲመራ ይችላል አሉ" ብለው ይከሱናል :: ከላይ እንዳልነው ሪቮሉሽኑ ከግቡ እንዲደርስ አመራሩ ከሠራተኛው ፓርቲ እጅ መግባት አለበት :: ግን በአንድ በተወሰነ ጊዜ ንዑስ ከበርቴው ሊመራ ይችላል" ወይ? ይህን ጥያቄ ይቻላል ወይም አይቻልም ብለው መመለሱ የነሱ ፋንታ ነው :: እኛ እስከዛሬ ድረስ "ከመጀመሪያ እስከመጨረሻው" በሠራተኛዊ ፓርቲ የተመራ ሪቮልሽን አላጋጠመንም :: ሁለተኛ ከበ ደግሞ የተያያዘ ጥያቄ ሳይሆን የሚታይን ነገር ማየት ወይም አለማየትን የሚጠይቅ ነገር ነው :: "ትግሉ እስካሁን የተመራው በንዑስ ከበርቴው ነው አሉ" ይሉናል :: የሠራተኛው መደብ ከመቸውም ይበልጥ አይሉ ተነስቷል ግን ትግሉን በግንባር ቀደምነት ያካሄዱት ምሁራን፣ አስተማሪዎቹ፣ አገር ወዳድ ወታደሮችና ተማሪዎች ናቸው :: እነዚህ ደግሞ መደባዊ መልካቸውን ብናየው ወደሠራተኛው ሳይሆን ወደንዑስ ከበርቴው የሚያዘነብሉ ናቸው

እነዚህ "ጓዶች" ክርክሩን በዚህ መልክ ማካሄድ ነበረባቸው :: በአንድ በተወሰነ ወቅት ንዑስ ከበርቴው ትግሉን ሊመራ ይችላል ወይ? ዛሬ በኢትዮጵያ የሚደረገውን ትግል በግንባር ቀደምነት የሚያካሄደው ማነው? የሚሉትን ቁም ነገር ያላቸውን ጥያቄዎች ረጋ ብለው እንደመመለስ "እንዲህ ስትሉ ማህበራችን SHOULE BE LED ያሉውን ውሳኔዎች ጥሳችኋል ብቻ ነው የሚሉን ::

ግን እኮ አመራሩን ለሠራተኛው መደብ "ስንጠይቅ" በመታገል ነው እንጂ እንዲህ "በትልቁ" እያደረግን የአውሮፓ ማህበር "ሹድ ቢ ሊድ" ብሏል፣ በተወሰነ መልኩም ስናየው እንደዚህ ነው፣ የፌደሬሽኑ ቡለቲን ቁ 6 ገጽ 3 ላይ ነገሩ "ጁፋ ሳይዘድ" ሆኗል፣ ወዘተ.

እያለን "በመከራከር" አይደለም :: ሠራተኛው መደብ ግንባር ቀደምነቱን በመራራ ትግል አስመስክሮ እንጂ አመራሩን የሚጨብጠው በማውራት አንዳይደለ ሌኒን ሲያስረዳቸሁ እንዲህ ይላል:_

" It is not enough to call ourselves the 'vanguard' the advanced contingent; we must act in such a way that all the other contingents recognize and are obliged to admit that we are marching in the vanguard.

ነገሩ እንዲህ ሆኖ ሳለ እንግዲህ ከፈለጋቸሁ ከአውሮጳና ከአሜሪካ ማህበራት ውሳኔዎች ጋር የጀመራቸሁትን "Petty bourgeois love story" ካሰናቸሁ ግፉበት :: እንዲያውም "ሹዱ ቢ ሲድ" የሚለው ውሳኔ መቼ፣ በስንት ደጋፊና ተቃዋሚ እንዳለፈ ሁሉ መዝግባቸሁ መረጃ ያቻቸሁን በጥንቃቄ አስቀምጧቸው :: የእግዜር ነገር አይታወቅም :: ወይም የግንባሩን አመራር እንደናንተው ከማህበሮቻቸን ውሳኔዎች ጋር "Love Story" ይዞ የሚወዘውዘው ንዑስ ከበርቴ እጅ ታገኙት ና መረጃቸሁን አቀርባቸሁ ትረካከቡ ይሆናል በርቱ፣

<u>ስለጊዜያዊ አጣዳፊ ተግበሮቻቸን</u>

ዛሬ ባለው በኢትዮጵያ ሁኔታ ተመርኩዘን ለቀ ስቀሳ /ለአጂቴሽን/ ተግባራቸን ምን አግጣጫ እንስጠው? እነዚህ ጓዶች ይህንኑ ጥያቄ በስድስት ነጥቦች "ዘርዝረው" ያስረዱናል: ዛሬ At this very moment" "Intensive agitation" የሚደረግባቸውን ነጥቦች ሊዘረዝሩ "ጎሳም ቱውትስ" ገጽ 17 ላይ የዘውዱ አገዛዝ እንዲጠፋ፣ እንዳለካቸው ተሰናብቶ ከህዝባዊ ምርጫ የወጣ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት እንዲቋቋም/?/ የህግ መንግሥት ጉባኤ የተባለው ወደ ህዝብ እንደራሴያቸ ጉባኤነት እንዲለወጥ /እንዲሁ በሰው/ ፖለቲካ እስረኞች እንዲለቀቁ፣ የህዝብ ፖለቲካል፣ ሶሻልና ኢኮኖሚ ጥያቄያቸ እንዲፈጸሙ፣ መሬት ሳራሹ እንዲሆን፣ የህዝብ ሰብዓዊና ዲሞክራቲክ መብቶቸ እንዲከበሩ መጠየቀ አለብን ይላሉ :: እንዲያውም ነገሩን ሁሉ አሳምረው ለመደምደም ለሰፊው ህዝብ በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መካከል፣ እንዲሁም ደግሞ በዲሞክራሲና በሶሻሊዝም መካከል ያለው ግንኙነት ሁሉ "Thorughly explained" መሆን አለበት ይላሉ ::

በጣም ግሩም ነው፣ ግን አሁንም አጣዳፊ ተግባሮቻቸን ለይቶ ለማየትና ለማሳየት ሆኖባቸሁ "That petty bourgeois diffisionss....." እያፈናቸሁ ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ላይ እንዳሳቸሁ ግልጽ ነው፣"Intensive agitation" አግጣጫ ብላቸሁ የምታቀርቧቸው ነጥቦቸ እንዲሁ "በደፈናው" ትክክለኛ ነጥቦቸ ናቸው :: ግን ታዲያ እንደዚሁ በደፈናው ከጀመራቸሁ አይቀር "at this very moment" ሰው ሰውን መጨቀኑን ለዘላለም እንዲያቆም፣ ስለሶሻሊዝም አስፈላጊነት፣ ስለኮሙኒዝም ጥሩነት፣ ወዘተ ለምን"Initeniveagitation" ይደረግም? እነዚህን መሪ ቃሎቸ እኛም እንቀበላቸዋለን :: እንዲህም በደፈናው እስከ ተወረወሩ ድረስ አንዳንዶቸን በደፈናው <u>መንግሥት ራሱ</u> ይቀበላቸዋል :: ልዩነቱ ግን እንዳለኪቸው ደሃን ሁሉ እኳ "ካሉ፪" ለህዝቡ ለማዘናጋት ይሞክራሉ:: እኛ ደግሞ እንደ እወረውርልታለሁ እያለ የህዝቡን ትጥቅ ለማስፈታትና;,<u>በገዛ ትግሉ</u> ብቻ ስለሆነ ህዝቡ በተቻለ ህዝብ ነፃነትን የሚጎናጸፈው ፍጥነት እንዲደራጅ "at this very moment" Intensive agitation ማድረግ አለብን እንላለን :: ህዝቡ በያለበት እየተደራጀ ትግሉን እንዲመራ የማገዙን ጉዳይ ከ"Intensive agiation" ፕሮግራማቸሁ ውስጥ ካላስገባቸሁት የናንተ በደፈናው የሚካሄደው "ቅስቀሳ" መንግሥቱ ራሱ ከሚያወጣው while paper በምን ይሻላል?? ነው ወይስ እነዚህን ጥያቄዎቸ ለማስፈጸም፣ መሬትን ሳራሹ ለማደላደል፣ ህዝባዊ መንግሥት ለማቋቋም፣ ባጭሩ <u>ሬቮሉሽን ለማድረግ</u> ከህዝቡ መደራጀት ይልቀ በናንተ "Intenive agitation" ይበልጥ ተስፋ አላቸሁ?

"ጓዶች" እንዲሁ በደፈናው ለህዝብ ነፃነት እንታገላለን ማለት በቂ አይደለም:: ሌኒንም ይላቸኋል "እንዲሁ በደፈናው ሪቮሉሽናዊ መሆን፣ በደፈናው ለሶሻሊዝም ለኮሙኒዝም መታገል በቂ አይደለም..... በአንድ በተወሰነ ጊዜ ባለ ኃይል እየታገሉ ከሁሉ አጥብቀው የሚይዙትን ጊዜያዊ ዓላማ ከዋና ዓላማ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል:" ቲዲያስ? እንደዚህም ስለሆነ "ህዝባዊ መንግሥት" ብሎ ዓላማውን የወሰነ ተራማጅ ዛሬ በ1966ዓ.ም. እዚህ ዓላማው ለመድረስ "ከህዝባዊ ምርጫ" በፊት "ህዝባዊ ፖርቲዎች" አያስፈልጉትም?

እና ያስፈልጊታል እንላለን:: እንዲያውም ይህ በፖርቲያች በጋዜጦች መቋቋም ላይ የሚደረገው Intensiveagitation' ከሁሉ ቀዳሚያ የሚሰጠው ተግባራችን ነው ብለን እናምናለን:: ይህ ጉዳይ በመጭው ጉባዔያችን ላይ ሰፊ ውይይት ሃሚደረግበት ስለሆነ እዚህ ላይ [illegible]

**ብዙም አንጸፍበት**

አሁን ወደሌላ እነዚህ ጓዶች ወደሚንቀትና ማህበራችንንም ወደሚከሱበት ወደ ሬፍርም ጉዳይ እንሂድ:: አጣዳፊ ጊዜያዊ ተግባር ሲባል የነዚህ ጓዶች የትግል ዘዴ ምን ያህል "ሾሳ በድፍንነት" እንደሚያጠቃው በዚህ በሬፍርም ጉዳዩ ላይ የሚያሳዩት ማወናበድ በቂ ማስረጃ ነው:: ከዚህም ሌላ በግልጽ ነገሮች ላይ በቁም ነገር መወያየት ምን ያህል እርማቸው እንደሆነ በዚህ በቀላሉ ጥያቄ ላይ ያሳዩት ሽፍጥና ከሪቮልሽናዊ መንፈስ የራቀ አሠራር ሳይወሳ መታለፍ የለበትም::

በዚህ ጉዳይ ላይ "የአውሮጳ መሪዎች" ተስፋ ቆርጠዋል" ሪቮሉሽኑን ከድተዋል" "ሪፍርሚስቶች ናቸው" እየተባሉ በማህበራችን ላይ በሚወረወሩት መሠረተቢስ ክሶች "የለሰለሰው" አሜሪካ ያለ አባል አሁን ደግሞ "የአውሮጳ መሪዎች በእንዳልካቸው መንግሥት ዕምነት ይኑረን ብለዋል፣ በደጋፊነት ተሰልፈዋል" ቢሉት በምንም አይደነቅም::ይህንን በአውሮጳ ሆነ በአገር ቤት ተራማጆች ዘንድ/ጨጽሄትቻችን በብዛት ያነባሉና:/ምንም ዓይነት ተቀባይነት የሌለውን በሬ ወለደ "የፈደሬሽኑ" ባለስልጣኖች ያለአንዳች ማስረጃ እንዲህ አያሉ ይደረድሩታል:—

"our right-opportunists have taken a completely new stand in the history of patriotic democracy(?) by being confident on Endalkatchew's regime, a well know stooge of U.S imperialists and an upholder of medieval autocracy, that it would bring political "reforms;"

ካሉ በኋላ ወዲያው ደግሞ "እና ማርክሲስቶች" እንደነሱ አይደለንም" ይማለት

"No matter how much our friends may be confident on Endalkatchew regime we believe the present regime is a government of aristocratic landlords and imperialist servants that can and will NEVER fulfill at least the basic demand presented by all the classesand social stratum LAND TO THE TILLER...."

ከፍ ብለን እንዳየነው ስለ 1966 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ሲጠየቀ ነገሩን በሌራ የገቡበት ሰዎች አሁን ደግሞ እዚህ ላይ ስለሬፍርም ሲጠየቀ ስለሪቮሉሽን በማውራት ሰው አደናግረው ለማለፍ እንደሚጥሩ ግልጽ ነው::

ጥያቄው እዚህ ላይ ግልጽ ነው:: የህዝቡ ትግል ገዥውን መደብ አንዳንድ ሬፍርሞችን እንዲያደርግ አስገድዶታል ወይስ አላስገደደውም? እና እስካሁን አንዳንድ ለውጦች ተደርገዋል እንላለን:: ይህም ከእንዳልካቸው የመጣ ስጦታ ሳይሆን የህዝቡ ትግል ያስገኘው ድል ነው:: **ስለነዚህ ሪፍርሞች አቋማችን ምንድን ነው? መልሳችን ግልጽ ነው:: ሪቮሉሽናዊ ትግላችንን**

ወደፊት ለማራመድ እንጠቀምባቸዋለን:: አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ የህዝቡን ትጥቅ አዘናግተው እን
ዲያስፈቱት እናጋልጣቸዋለን:: " አንዳንድ ሰዎች" ይላል ስታሊን "አንዳንዶች ሰዎች ሌኒኒ
ዝም ሪፎርሞችን በጠቅላላው የሚቃወም ይመስላቸዋል:: ይህ ግን ፈጽሞ ስህተት ነው::"

የኛ "ማርክሲስቶች" ግን እዚህም ላይ ነገር በማምታታትና በአፈጮሌነት ብቻ ለማምለጥ
ይሞክራሉ:: ማንም እንደሚያውቀው፣ "ማርክሲስቶቻችንም" እንደማይስቱት አስር ዓመት ሙሉ የኢ
ት. ተማሪዎች በጀግንነት የተዋጉለት "መሬት ላራሹ" የሚለው መሪ ቃል ሪፎርሚስት መሪ ቃል
አይደለም:: ሪቮሉሽናዊ መሪ ቃል ነው:: እንደዚህም ስለሆነ "የአንዳልካቸው መንግሥት ሪፎ
ርም ሊያመጣ ይችላል ወይስ አይችልም?" ብለው ሲጠየቁ ነገሩን"emphasize"አያደረጉ "እንዳ
ልካቸው ሪቮሉሽን ሊያደርግ አይችልም፡" ብለው ያለ ተጠየቁትን ሲመልሱ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን
ያሰኛል:: አንደኛ እንኳን እኛና አንዳልካቸው ራሱ ሪፎርም እንጂ ሪቮሉሽን አደርጋለሁ ብሎ
ስላልተናገረ እነዚህ ሰዎች "የአንዳልካቸው መንግስት ሞት ቢመጣ መሬት ላራሹን ከሥራ ላይ
አያውልም" ሲሉ የጠራ ሜዳ ላይ ከገዛ ጥላቸው ጋር ትግል የገጠሙ መሆናቸው ግልጽ ነው::
እንደዚህም ያል ተጠየቁትን ሲመልሱ "ከዝሆንና ከአንበሳ ማን ያሸንፋል" ቢለው "ነብርን ማን
ችሎች ብሎ" የመለሰውን" የዋህ ያስመስልባቸዋልና ዝምቢሉ ይሻላቸዋል:: ሁለተኛ ነገር ደግሞ
እንዲህ ዳርዳሩን ሲያንዣብቡ ስለነዚህ ሪፎርሞች ምን አቋም እንዳላቸውና ምን <u>አቋም መውሰድ</u>
እንደሚያስፈልግ ስለማይናገሩ በግንባር ቀደምነት ሳይሆን "በስጋጃቸን" የተሰለፉ አዲስ ዓይነት
"ማርክሲስቶች" ሃገራችን አፍርታለች ማለት ነው:: የምስራች፡

ስለጊዜው ተግባራችንና ስለሪፎርሞቹ ጉዳይ መነገሩን የሚያሳየው ግንባሯ ቀደም የሚፈልግ
ሰው ካለ በኢዜና መሪዎች በኩል አጠያይቀ ብለን አንመክረውም:: የፈደረሽኑ ባለስልጣኖች <u>ሽሽ
ተው</u> ያመለጡት የመሰላቸውን ዋና ጊዜያዊ ጥያቄ የኢዜና መሪዎች ደግሞ ሰው በማደናገር ብርታት
ሊዘሉት ይፈልጋሉ:: በያለበት የሪፎርም ጉዳይ እየተደጋገመ ቢጠቀስም "ሰም ቶውቶስ" ላይ ጉዳ
ዩን እንደ ገጽ 9 "የሚያብራራው" ያለ አይመስለንም:_

መጀመሪያ እዚሁ ገጽ ላይ ሪፎርም እንዳለ ብቻ ሳይሆን "እስከ ታሪካዊ አመጣጡ"
ሲያስረዱን:_

"Intimidation soon gave way to concession, and concessionled to a chain of other concessions......"

ይሉና መለስ ብለው ደግሞ ነገሩን ሲያጠፉብን:

"No one should entertain the notion that the exploiters of yesterday can be the reformers of today......."

ብለው የምንይዘው የምንለቀው ያሳጡናል:: እንዲህ ግራ አጋብተው ደግሞ ገና መልሰ
ነፍስ ሳይዘራብን እንደገና "አይቻሉም" አይመጡም" የሚሏቸውን ሪፎርሞች እንዴትና ለምን እን
ደተቻሉ የአንዲት መስመር እንኳን ፋታ ሳይሰጡ:

"No one should expect that the concessions are charitable handouts like imperial alms. The rulling class wants to save the whole by conceding the parts."

እያሉ በነፍሳችን ይጫወቱብናል:: በዚህ መልክ አንዴ ከእሳት ወደ በረዶ፣ አንዴ ከበ
ረዶ ወደእሳት እየጨመሩ የቀምስቀሉን የሚያሳዩትን አንባቢ ደግሞ አንዳንዴ ከመሃል "ሲያዋልሉት"
ነገሮ Confuse" ለማድረግ ሲሆን የኛ "ማርክሲስቶች" ከላዩ የወረደ ልዩ ስጦታ አላቸውና:

"The significance of these conscessions shall not be fated to meet a response as if nothing has changed"

ብለው ሰው አደናግረው ቀጭ ይላሉ:: እንግዲህ በዚህ ዋና ጉዳይ ላይ ምን እንደሚያስጡ ራሳቸውም ስለማያውቁት ምን መስራት እንዳለባቸው ሊያውቁ አይችሉም:: ያው መደናበር ሊመጣ ነው:: ለወጉ ግን ደግሞ አንዱ ገጽ ላይ እነዚህን ሪፎርሞች ለማጋለጥ መታገል እንዳለባቸው ይነገሩናል:: ለምን ማጋለጥ ብቻ ይሆናል? በነዚህ ሪፎርሞች መጠቀም የመሰለውስ ዋና ነገር? እንዲህ ብለን እንጠይቃቸውም የማንወጣበት ማጥ ውስጥ ይዘውን እንዳይገቡ:: ስለማጋለጡ ግን ለወጉ እንዲህ ይላሉ:_

"The congress reiterated ESUNA's determination to intensify agitational work using various means to expose ruling class deceptions that are designed to dampen the rising revolutionary tide."

ለወጉ ያልነው ለምንድን ነው? ባጭሩ በዚህ በኩል "የአጅቴሽን ትግል"፣ ማፋፋም፣" "በአዲስ ዘዴ መጠቀም" እያሉ ለፈ[illegible] ያሳቸውን አቋም እንኳን ገና አጣርተው አልተናገሩም፡ ደግሞስ እስካሁን አንባቢን እንጠይቀው የትኛውን ሪፎርም ሲያጋለጡ ታይተዋል? ፓርቲ ሳይቋቋም፣ ህዝባዊ ድርጅቶች ነፃ ጋዜጦች ሳይኖሩ "ጊዜያዊ" መንግሥት ይቋቋም ሲሉ እንደያውስ ያለአዳንዳች ማጋለጥ በሪፎርም እንጠቀም፣ ሪፎርሚስት እንሁን ማለታቸው አይደለም?

የአጅቴሽን ትግል "ማፋፋም" በአዳዲስ ዘዴያች መጠቀም እያላችሁ ተጮሃላችሁ:: የሃገሪቱን ሁኔታ መቼ በወጉ ተከታተላችሁ:: አባሎች ሳይንሳዊ ትንተና እንዳያደርጉ መቼ ስለሁኔታው መረጃዎችን የመሰብሰብና የማቀረብ ሃላፊነታችሁን ፈጸማችሁ? ሌላው ቀርቶ ማህበራችን የሚያስናዳቸውን መረጃዎች እንኳን /ትግላችን ዜናን ለምሳሌ/ መቼ አባዝቶ ማደል ሆነላችሁ? ታዲያ በምን ላይ ተመርኩዛችሁ የአጅቴሽን ትግሉን ታፋፍማላችሁ? ነው ወይስ "የዘውዱ አገዛዝ" ደውደም "ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ይስፋፋ" ለኢትዮጵያ ህዝብ" በሶሻሊዝምና በዲሞዝራሲ መሃከል ያለው ግንኙነት throughly explained ይሁንለት" ስላላችሁ ትግላችሁ ከአምናው ዘንድሮ የተፋፋመ መስሏችሁ ይሆን? ከዚህ በተጨማሪ ከአምናው "ያፋፋማችሁት" ነገር ቢኖር በማህበራችን ላይ የያዛችሁት የመሠረተቢስ ክሶች ጋጋታ ነው:: "በአዳስ ዘዴ" ስትጠቀሙ ያየናችሁ የፖለቲካ ክርክር ቢያልቅባችሁ በቀርብ ምስራቅ ማህበራት ውስጥ ደብዳብ ስታስነሱና "የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር በቀ/ምሥራቅና በአፍሪካ" እንዳይቋቋም ያል ተሰካ መፍጨርጨር ስታደርጉ ነው:: "አዲስ ዘዴ" ያየነው በዲሞክራሲያዊ ትግል ከትግሉ መነጠል ያቃታችሁን ጓዶች የአንዱ የምስጢር ድርጅት አባልናቸው እያላችሁ ለፖሊስ ስታስረክቧቸው ነው:: እዚቸው ኢዙና "ልዩ ጉባዔ ላይ እንኳን" የጽናንተን ባደ "ሳይንሳዊ ትንተና" አቀርባችሁ ሳትጨርሱ መሠረተቢስ በሆኑ ክሶች በመወንጀል በአገር ቤትና በአሜሪካ የሚገኙትን አገር ወዳዶች በአውሮጳ በሚገኙ ወገኖቻቸው ላይ ለማነሳሳት ስትሞክሩ ነው የታያችሁት:: እንዲህ አርጌም የለ ትግልን "ማፋፋም" እንዲህ አርጌም የለ "በአዲስ ዘዴ መጠቀም" ብራቮ፡ በርቱ፡

ዋና ጥያቄዎች በማመስሉን በድርጅቶችና በሪፎርም ጉዳይ የኢዙና የፌዴሬሽኑን አቋሞች እየጠቀስን እኛ የምናምንባቸውን መስመሮች ለማሳየት ሞክረናል:: የጊዜውን ተግባራችንን በሚገ፺ ካወቁን ምንም ከሃገራችን ርቀን ብንገኝ ትግሉን በተጨባጭ መንገዱ በመርዳት ብዙ ልንሠራ እንችላለን ብለን እንገምታለን:: ለዚህ ግን ከሁሉ አስቀድሞ አድርባዩችና አናርኪስቶች በንቀናቂያችን ውስጥ የሚነዙት ውዥንብር የግድ መገታት አለበት:: ይህንንም ማድረግ የሚቻለው ግለሰቦች ላይ በመረባረብ ሳይሆን የፖለቲካ አቋምን ብቻ በመተቸት ስለሆነ የመሰሉንን አስተያየ

ቶች እነሆ አስፍረናል::

ማህበራችን በነዚህና በሌሎችም አጣዳፊ የፖለቲካ መስመር ጉዳዮች ላይ በጽሞና ተወያይቶ አድር ባዮች የሚረጩት ውዥንብር በቅርቡ እንደሚጣራ እንጠራጠርም:: ይህም በመጭው ጉባኤያችን ላይ እነዚህ ግለሰቦችና ቡድኖች ከፖለቲካ ክርክር እየሸሹ በትርኪ ምርኪ ጊዜ እንዳያሳልፉ ነቅተ መጠበቅ የእያንዳንዱ አባል ግዴታ ነው::

ብርሃኔ ደመቀ

## ማመሳከሪያዎች

1. Ethiopian Herald, January 22, 1970
2. Some thoughts on the current Situatia In Ethiopia E.B. of Esuna P. 31
3. V.I. Lenin "Left Wing" Communism -an infantile disorder Novosti Press Agency
4. News Letter Published Guarterly by the N;Y. Chapter Esuna Dec. 1970
5. V.I. Lenin What is to be done?
6; V:I. Lenin "Left Wing Communism p. 37
7. " Some thoughts on the current Situation In Ethiopia p. 27
8. Ibid p. 29 - 31
9. ታህሳስ 20 የወጣ ሰማዕታት መታሰቢያ ቀን ዓለም አቀፍ የኢት. ተ. ማህበር መግለጫ በአውሮጳ የኢት. ተ.ማ. የዘጋጀ ታህሳስ 20,1963
10. News letter see 1971
11. Struggle, vol. 1 No 4 June 1971

12. "Some thoughts......" Struggle vol. 1N° 4 June 1971
13. News letter vol.1 N°2 dec.970.
14. The historical destiny of the doctrine of K.MARX v.1 Lenin CU works o vol. 18 oY 584.
15. "Some thoughts....." P.15
16. J. Stalin Principles of Leninism Peking 1969 p.87
17. K.MARK a brief Biographical Sketch with an Exposition of Markism V.I. LEnin Coll; works Vol. 21 p 75
18. Bulletin of the world wide Federation of Eupoian Student vol.1?N°6
18 bis Some thoughts p 31
19. Challenge vol XIII N° 1 August 1973 p. 24
2o. "Some thoughts ...." p. 5
21. Ibid p. 3o.
22. Lenin what is to be done? p. 53
'Bulletin..." vol I N° -
24. Ibid.
25. VI Lenin 'Left' ving Communism...." p. 6o 25bis Bulletin N°-6
26. "Some thoughts..." p.32
27. "Bulletin..."VolI N° 6
28. Ibid 28 Ibid 3o Lenin what is to be done? p. 83
31. Ibid p.79 32 Ibid 81
34. Ibid
35. "Some thoughts..." p.3